

ስብሪው ስየኖሪ ስለመተዋወቅ

አንድ ጊዜ ከሠላሳ ዓመት በላይ፣ በጋብቻ ዓለም ውስጥ የቆየ የታወቀ አገልጋይ፣ እንዲህ አለ። «አብዛኛዎቻችሁ እንደምታውቁት ፣ እኔና ባለቤቴ ከተጋባን ሠላሳ ዓመት አልፎናል። በእነዚህ ዓመታ ት ውስጥ ብዙ ደግና ክፉ ዘመናት ገጥመውናል። ጌታ አምላካች ንም በልጆች ባርኮናል። ይሁን እንጂ እኔና ባለቤቴ አስካሁን ድረስ በደንብ አልተዋወቅንም። ያለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት፣ እርስ በርላችን ለመተዋወቅ፣ በር የተከፈተልን ይመስለኛል» በማለት፣ ስ ብከቱን ሲቀጥል፣ ብዙዎቻችንን በመገረም ተሞላን። ስለዚህ እኛ ም በፋንታችን የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅና መወያየት ጀመር ን። እንዴት ሳይተዋወቁ ሠላሳ ዓመት አብረው ኖሩ? ከማያውቃት ሚስት ልጆችን ለምን ወለደ? ሚስቱን ሳያውቅ እንዴት አገልጋይ ሆነ? የሚሉትን አወጣንና አወረድን።

ይሁን እንጂ አሁን ሳስተውለው፣ ስባኪው የተናገረው ብዙ እ ውነትነት ነበረው። መተዋወቅ ሲባል፣ ሙሉ በሙሉ መነባበብና ራቁት መሆን፣ የሚለውን ጽንሰ አሳብ በመያዙ ነው። <u>የመንፈስና የነፍስ፣ እንዲሁም ፍጹም የሆነ የሥጋ ውህደት፣</u> በሁለቱ መካከል እስኪፈጠር ድረስ፣ አንድ ሆኑ ለማለት እያስደፍርምና። የስውዬ ውም ትልቁ ችግር፣ ወደ ፍጹም ውህደት አለመምጣታቸው ነበር እንጂ፣ ሳያውቃት አብሯት ኖረ፣ ወይም አገባት ለማለት አይደለ ም። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን የመሰለ እንድ ታሪክ፣ በዘፍ. 29:25 ላይ ይነግረናል።

«በነጋም ጊዜ እነሆ ልያ ሆና ተገኘች ላባንም ምነው እንደዚህ አደረክብኝ? ያገለገልሁህ ስለ ራሔል አልነበረምን?» ለምን አታለልኸኝ? አለው።

አታላዩ ያዕቆብ በላባ ተታሎ፣ የማይፈልጋትንና የማይወዳትን ልያን በጨለማ አግብቶ፣ ሌሊቱን ሁሉ የልቡን ሲያጫውታት አደረ። አርግጠኛ ነኝ በሌሊት የጫጉላ ጨዋታው፣ ስለ ልያ መጥፎ ነትና ስለ ራሔል ቁንጅና ያለውን አመለካከት በሰፊው እንደነገራት። ከዚያም አልፎ ሰባት ዓመት የተገዛሁልሽ ላንቺ ለራሔል ነበር። እነሆ፡- ዛሬ ህልሜ ሁሉ ተፈጸመልኝ፤ እያለ እምላኩን ሳያመሰግን እንዳልቀረ እገምታለሁ። የሚገርመው ግን የተጨፋፈነውን የሚገልጥ ብርሃን መምጣቱ ነው።

ሚት በነጋ ጊዜ ሙሽራትን ሲያያት፤ ልያ ነበረች። የተጠላች ው የማትፈለገው። ጭራሽ በያዕቆብ፣ በህልሙም በውኑም ያልታሰበ ች። ያዕቆብ በንዴትና በአልሀ ተሞልቶ፣ ወደ ላባ በመሄድ፣ ለምን አታለልኸኝ? እንዴትስ በሕይወቴ ላይ ትቀልዳለህ? የማልፈልጋትን ና የማልወዳትን ለሚስትነት እንዴት ትሰጠኛለህ? በማለት በላባ ላይ እንደተቆጣ መጽሐፍ ቅዱሳችን ይገልጸልናል።

መቼም በእኛ ዘመን፤ መልኳን ሳያዩ እንደ ያዕቆብ አያገቡም። ይሁን እንጅ፤ ብዙ የተደባበቁና የተሸፋፈኑ ሚስቶችን /ባሎችን/ በማግባት፣ ወይኔ እንዴት ተታለልኩ? ለምን ቸኮልኩ? እርሷን/ አርሱን ባየሁበት ቀን እግሬ በተሰበረ? በጣም ተሞኘሁ፤ ትልቅ ጥፋት ነው ያጠፋሁት? በማለት፣ በጋብቻቸው ያልረኩና የሚጸጸቱ ብዙ ያዕቆቦች፤ ዓለምን እንደሞሏት ግልጽ ነው። የሚገርመው ግን እነዚህ ያዕቆቦች፣ ዓለማውያን ብቻ ሳይሆኑ፣ በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ መብዛታቸው ነው።

የዳኑና የጌታ እውነት የበራላቸው በትዳራቸው መታለላቸ ውና፣ በየቀኑ የሰቆቃ ድምጽ ማሰማታቸው፣ ለብዙዎቻችን እንቆቅ ልሽ ሳይሆንብን አልቀረም። በተለይም ከባሕር ማዶ የሚደረገው

ጋብቻማ፣ በአብዛኛው የተሸፋፈነ ሕይወት የሞላበት ነው። ልጅ ወልዳ እንዳልወለደች፣ ሚስት ፈትቶ እንዳልፈታ፣ የሚሆኑት ጥቂቶች አይደሉም። አንዳንዱም ሚስትና ልጆቹን በአገር ቤት አስቀምጠ፣ ያላገባሁ ድንግል ነኝ በማለት፣ ተሞኝቶ የሚያሞኝውን አታላይ ቤቱ ይቁጠረው።

ከእግዚአብሔር ቃል እንደምንማረው፣ ትዳር ክቡርና የተቀደሰ በመሆኑ፣ በግልጽነት መሠረቱ እንዲጀምር ያስፈልጋል። የመጀ መሪያዎቹ ተጋቢዎች፣ አዳምና ሔዋን፣ በገነት ጋብቻቸውን ሲመሰ ርቱ፣ በፍጹም ግልጽነት ነበር። «አዳምና ሔዋን ራቁታቸውን ነበሩ አይተፋፈሩም ነበር» በማለት፣ የዘፍጥረት መጽሐፍ የእውነተኛውን ጋብቻ ሕይወት ይገልጽልናል። ዘፍ. 2:25

ዛሬም ቢሆን፣ ጋብቻ ሊመሰረት የሚገባው፣ በግልጽነት መን ፈስ ነው። እያንዳንዱ ባል /ሚስት/ ከማታለል ሕይወት በመውጣት እውነተኛውን ባህሪያቸውንና ማንነታቸውን መግለጥ ይገባቸዋል። ሰ ዎች ራሳቸውን ግልጽ አድርገው ካልቀረቡና ለመነበብ ፈቃደኛ ካል ሆኑ፣ የቋንቋ መደበላለቅ በትዳራቸው ላይ እንዲፈጠር ጥርጊያ መ ንገድ ይከፍታሉ። በአንጻሩ ደግሞ፣ ለመነበብ ራሳቸውን ግልጽ አድ ርገው፣ ልባቸውን የሚከፍቱ ሰዎች፣ በቀላሉ ፈውስን ለቤተሰባቸው ያመጣሉ። የ<u>ቃል ኪዳንም</u> መመሪያው አንዱ ይህ ነው።

ጋብቻ በቀላሉ የማይበጠስ፣ ትልቅ የሕይወት ገመድ ነው። የእግዚአብሔር ማንነት አብሮ ስላለበት፣ በቀላሉ የሚታለፍ ጉዳይ አይደለም። ልብ በሉ፦ አታላዩ ያዕቆብ ስሙና ታሪኩ የተቀየረው፣ በጽንኤል እውነተኛ ማንነቱን ከገለጸ በኋላ ነው። ተሸፋፍኖ በረከት አይመጣም። እንደበታችሁ ተከፍቶ፣ የውስጥ ማንነታችሁን፣ ለትዳር ጓደኛችሁ እንድትነገሩ ያስፈልጋል። ቃል ኃይል አለው ይፈውሳል። ምናልባትም ዛሬ እናንተ፣ እንደ ያዕቆብ ታሪካችሁን ለመቀየር የያ ቦቅ ወንዝ መሻገር ላያስፈልጋችሁ ይችላል። ይሁን እንጂ፦ የመን

ፈስ ቅዱስ ወንዝና፣ የጐልጐታው መስቀል/ጵንኤል/ ግን፣ ለትዳራች ሁ ያስፈልጋችኋል። ዘፍ. 32:32

ወገኖቼ! የዘመናችን መፈወሻና ስም ማስቀየሪያ፣ ድል አድ ራጊው የሹኣ/ አየሱስ/ ብቻ ነው። በእርሱ አጅ ውስጥ፣ ሁሉንም አ ይነት በሽታና ችግር፣ የሚያስወግድ ሁለገብ ቁልፍ /መድኃኒት/ አለ። ያም ደግሞ፣ ከቡር ደሙና መንፈሱ ነው። ክርስቶስን ወደ ት ዳራችሁ ከጋበዛችሁትና፣ ለመታከም ፈቀደኛ ከሆናችሁ፣ በቀላሉ ለ ትዳራችሁ ፈውስ ይበቅልላችኋል።

ለእናንተም ሆነ ለልጆቻችሁ፣ አውነተኛ በረከት መፍለቅ የሚ ጀምረው፣ በግልጽና በእውነት እርስ በእርሳችሁ፣ መመካከር ስትጀ ምሩ ብቻ ነው። እርግጥ ነው፣ በአጭኛምነት አያላችሁ፣ ብዙ ተደባ ብቃችሁ ሊሆን ይችላል። አሁን ግን፣ አዲስ ሕይወትና ጉዞ ላይ በ መሆናችሁ፣ እንደ ያዕቆብ ማንነታችሁን መግለጽ ጀምሩ። የኋላዬን እየተውኩ፣ ወደ ፊቴ ያለውን ለመያዝ አዘረጋለሁ ነውና። በአዲስ የግልጽነት መንፈስ ጉዞ ጀምሩ። ይህ ካልሆነ ግን፣ ሁከትና ጭንቀ ት በቤታችሁ እንሚበዛ አትዘንጉ። የጋብቻችሁ መጀመሪያና መነሻ ደግሞ፣ ለፈውስና ለፍቅር፣ መሆኑንም አትርሱ። <u>ጋብቻ በቃል ብቻ የሚገለጽ አይደለም። በተግባር የሚተረጉም የሚታይና የሚኖሩት ሕይወት ነው እንጂ። ስለዚህ በየቀኑ ግለጹት፣ ኑሩበት።</u>

በ1993 /አ.ኤ.አ./ ግብጽ ውስጥ ካይሮ ነበርኩና አንድ እውነተ ኛ ታሪክ፣ ግብጻዊው መጋቢ ጓደኛዬ አጫወተኝ። በግብጽ ባሕል መሠረት፣ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ፣ ለአባሎቹ ሚስት/ባል/ ማጨት የተለመደ ነው። ታዲያ አንድ ጊዜ ፓስተሩ፣ በጣም ለሚወደው የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ፣ አንዲት ሴት አጨለት። መጋቢው ል ጅቱን የመረጠበት አንደኛው ምክንያት፣ ሁልጊዜ የቤተ ክርስቲያን ደምበኛ በመሆን ቀርታ ስለማታውቅ። ሁለተኛው ደግሞ፣ መልከ ቀና ቆንጆ በመሆኗ— ሦስተኛም በሚያያት ጊዜ፣ የረጋችና ደርባባ ስለመሰለችው መልካም ሚስት ትሆናለች በማለት አጨለት።

እንደ ባሕላቸው ወግ፣ ፓስተሩ ሌሎችን ሽማግሌዎችና፣ የታጨላትን ልጅ በመያዝ ቀጠሮ ይዘው ወደ ልጅቱ ቤተሰብ ሄዱ። ቤተሰቦቹም በደስታ ከተቀበሏቸው በኋላ፣ የለስላሳ ግብግ ተደረገ ላቸውና፣ ምርጫቸውን ተጠየቁ። በምርጫቸው መሠረት፣ ለስላሳዋ ን በዝርግ ሳህን አዘጋጅታ፣ ነጭ ልብሷን ለብሳ ወደ ሳሎን በፈገግ ታ፣ የታጨችው ሴት ብቅ አለች። ወጣቱም ስለ ልጅቱ የሰማው እውነት መሆኑንና አለመሆኑን ለማወቅ ፈለገ። ስለዚህ ለስላሳውን ይዛለት ወደ እርሱ ጠጋ ስትል፣ ሳታስበው ቀስ አድርጉ ሳህኑን ሳብ አደረገው። ይህን በሚያደርግበት ጊዜ፣ ለስላሳው በለበሰችው ነጭ ልብስ ላይ በሙሉ ተደፋ። ወዲያውም፡- ማለሽ /ይቅርታ/ ሳላ ውቅ ነው በማለት፣ በዓረብኛ ተናገረ። ሁሉም ለጊዜው ቢደናገጡ ም፣ ልጅቱ ምንም አይደል ብላ ወደ ጓዳዋ ተመለሰች። ከዚያም ከ አስር ደቂቃ በኋላ፣ ልብሷን ቀይራ እየሳቀች መጣች።

ወጣቱ የወሰደውን እርምጃ፣ በፈገግታ ስለተቀበለች፣ በእርግ ጥም ይህቺ ወጣት ትዕግሥተኛና አስተዋይ ናት በማለት፣ የመጋቢ ውን ምርጫ በመቀበል፣ ለማግባት ወሰነ። ታዲያ የእውነተኛው ባህ ሪ መፈተኛ፣ ጋብቻ ተጀመረና አብረው ጥቂት ወራቶች በደስታ አሳለፉ። ይሁን እንጂ ቀስ በቀስ፣ ባህሪዋ እየተቀየረና በሆነ ባልሆ ነው እየተነጫነጨች መሄድ አዘወተረች። የማያስቆጣው ያስቆጣ ታል። ሲናገራት ቀና መልስ አትመልስም። ቤታቸው ከደስታ ቤት ይልቅ የጭቅጭቅና የሃዘን ቤት ሆነ።

አንድ ቀን ይህ ወጣት፣ ምክንያቱን ለማወቅ ስለፈለገ፣ እን ዲህ አላት። «እህቴ ምን ነካሽ? ጠባይሽ በጣም እየተቀየረ መጣ ሳ? ቤታችንም እኮ ሲኦል መሰለ? እኔ ከመጀመሪያውም ስለማላ ውቅሽ፣ ይህ እንዳይሆን ብዬ ፈርቼ ነበር። ትዝ ይልሽ ከሆነ፣ በመ ጀመሪያው ቀን ከሽማግሌዎች ጋር ወደ ቤትሽ የመጣን ጊዜ፣ ለስላ ሳውን ቀስ ብዬ ወደ ልብስሽ ያፈሰስኩት፣ ትዕግሥትሽንና ይቅርታ

አድራጊነትሽን፣ ለማየት እውቂ ነበር:: ታዲያ በዚያ ቀን ያሳየሽው ጨዋነትና፣ አሁን ያለሽበት ባህሪይ፣ የስማይና የምድር ያህል ተራርቋል:: ምክንያቱ ምንድን ነው?» በማለት ዓይን ዓይኗን እየተ መለከ ጠየቃት::

ወጣቷም በቀጥታ መልስ ከመስጠት ይልቅ፣ ድንገት ከመ ቀመጫዋ ብድግ አለችና፣ ወደ ልብስ ማስቀመጫዋ ቁም ሳጥን ሄደች:: በእጇም የተቦጫጨቀና፣ በለስላሳ የተበላሸ ነጭ ልበስ፣ አን ጠልጥላ ይዛለት መጣችና በፊቱ ቆመች:: ወጣቱም በመገረም ምን ድን ነው ይኼ? በማለት ጠየቃት:: ይህ ቀሚስ ያን እለት የለበስ ኩት ነው:: አንተ ለስላሳውን በደፋህብኝ ጊዜ፣ ከመናደዴ ብዛት የ ተነሳ፣ ወደ ክፍሌ ገብቼ፣ በጥርሴ፣ በእጄና በእግሬ የቦጫጨኩት ነው:: ከዚያ በኋላ ነው ንዴቴ በርዶልኝ ልብሴን ቀይሬ ወደ አናን ተ ተመልሼ የመጣሁት አለችው::

ወጣቱም ይህን ሲሰማ፣ በታላቅ ድንጋጤ ውስጥ ገብቶ፣ በደ መ ነፍስ እንዴ! እንዴ! አለ፣ ሳያስበውም:- ይህችማ ልብሷን እን ዲህ አድርጋ ከቦጫጨቀችው፣ ነገ ለእኔም አትመለስም::ወይ ጉዴ! በማለት ድምጹን ከፍ አድርጐ ጮኸ:: ሴቲቱም እጠገቡ ቆማ ስለነ በር፣ ጠባይህ ካላማረ የት ይቀርልሃል? አለችው ይባላል:: ታሪኩ ተ ረት ሳይሆን፣ እውነት የተፈጸመ ነው:: ዛሬስ ይህን በመሰለ የድብ ብቆሽ ሕይወት የተጋባው ሰው ምን ያህል ይሆን?

ጠቢቡ ሰለሞን በምሳሌ 19:13 «ጠበኛ ሚስት እንደማያቋርጥ ነጠብጣብ ናት» በማለት የደረሰበትን ይናገራል:: ሁልጊዜ ችግሩ በ አህቶቻችን ብቻ አይደለም:: ወንዶችም ቢሆኑ ለመጨቃጨቅ አይ ሸነፉምና:: በዚህ አጋጣሚ በዚያው በካይሮ የሰማሁትን፣ ሌላውን ታሪክ ልግለጸው:: ይኼኛው ችግር በወንዱ ላይ ስለሆነ፣ አድልኦ አ ንዳላደረኩ እህቶች ሊረዱኝ ይችላሉ ብዬ እገምታለሁ::

ሁለቱ ሙሽሮች በጉባኤ ፊት፣ የቃል ኪዳን ስነ ስርዓታቸውን ፈጸሙ። ከዚያም በተዘጋጀው ድግስ፣ ከተዝናኑና እንግዶቻቸውን ከሸኙ በኋላ፣ ማታ ወደ ተዘጋጀላቸው የጫጉላ /ሃኒሙን/ ቤት አመሩ። ቤቱ ፎቅ ስለነበረ፣ ሙሽሪት ደረጃውን እየወጣች፣ ፊት ለፊት እየመራች እያለች፣ ቬሎው ያደናቅፋትና፣ ልትወድቅ ትንገዳገዳለች። ወንድ ሙሽራ ወዲያውኑ፣ እኔን! ብሎ ቀና አድረጉ ያነሳና ደግፎ ወደ ቤቱ ይገባሉ። ላምንት በጫጉላ ቤታቸው ከቆዩ በኋላ፣ ወደ መኖሪያ ቤታቸው ለመሄድ ተነሱ። ሙሽሪት አሁንም ረጅም ቀሚሷን ለብሳ፣ ደረጃውን ቀስ እያለች ተጠንቅቃ መውረድ ጀመረች። ነገር ግን፣ ያደረገችው ታኮ ጫማ ነበርና፣ ሳታስበው አደናቅፏት ወደቀችና፣ ትንሽ ተጐዳች።

ባልየው በጣም በመናደድ፣ "ይድፋሽና አስተውለሽ አትራመጂም እንዴ? የት ልትደርሽ ነው እንዲህ የምትጣደፊው" በማለት ተቆጣት። ከላምንት በፊት እኔ ልደፋ በማለት የደገፈኝ፣ ምነው ከስባት ቀናት በኋላ ጠባዩ ተቀየረ? በማለት፣ በምርጫዋ በመሳሳቷ በጣም አዘነች። ወንድ ከሠርጉ ማግስት የአስር አመት ያህል ወደ ኋላ፣ ስለሙሽሪት ያለው አስተሳሰብ ያረጃል ይባላል። ማለትም ከጋብቻ በፊት የነበረው ፍቅርና አቀባበል፣ በጣም በመቀነስ ቀዝቃዛ ይሆናል። አባባሉ ልብ ወለድ ስለሆነ፣ የማመንና የመቀበል ግዴታ የለባችሁም። ነገርን ነገር ወልዶት፣ የጨመርኩት አሳብ ነውና።

አዎ ዛሬም በዘመናችን፣ በእጮኝነት ጊዜያቸው፣ እየተቅለሰለሱ እንደ ቋቋቴ ውኃ፣ የፍቅር ድምጻቸውን ብቻ እያስተጋቡ ቆይተው፣ እህቶችን በማታለል ያገቡ ሞልተዋል። እነዚህ ሰዎች፣ ግብረ ሥጋን ለመፈጸምና ለጊዜያዊ ደስታ የቋመጡ እንጂ፣ ዓላማ ያላቸውና በተግባር የተፈተኑ አይደሉም። እንኳን ለትዳር፣ ረጅም ጉዞ ሊጓዙ ቀርቶ፣ ለጓደኝነትም አይመቹም። ሕይወታቸው በአሸዋ ላይ ስለተመሠረተ፣ ጭንቅ አይችሉም። በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጡ፣ ሃሞታቸው የፈሰሰ፣ ወኔ የሌላቸው ደካሞች ናቸው። ስለነዚህ ዓይነት ሰዎች፣ መጽሐፍ ቅዱሳችን ሲናገር፣ «ወስላታን ሰው በመከራ

ጊዜ መተማመን፣ እንደ ተሰበረ ጥርስና እንደሰለለ አግር ነው» በማለት ይገልጻቸዋል። ምሳሌ 25፣19

ይህንን የመሰለ ድብብቆሽ የሞላበት ትዳር፣ በየቦታው ይገኛ ል። በተለይ በሰለጠነው ዓለምማ አይወራ። የባንክ ሂሳባቸውን የሚ ይዙት ለየብቻ፣ ዓላማና ዕቅድ የሚቀይሱት ለየብቻ፣ የቤት ወጪ ስንኳ ሳይቀር፣ የሚወስኑት ለየብቻ ነው። ውይይታቸውን በመጻጻፍ በወረቀት የሚያደርጉ፣ መደማመጥና መተማመን ያልቻሉ፣ እጅግ ብዙዎች ናቸው። ልጆች ይወለዳሉ፣ እነርሱም የወላጆቻቸውን ባህሪ በመያዝ ያድጋሉ። ትልቅ ሲሆኑ፣ ለአገርና ለሕዝብ እንቅፋትና ሸክም ይሆናሉ። አብረው እየኖሩ አለመተዋወቅ፣ ሳይስማሙ አብሮ መጓዝ፣ ትልቅ እርግማን በመሆኑ፣ ትውልድን ይበክላል። አሞጽ 3:3 እንዲህ ብሎ ይጠይቃል። «በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ በአንድነት ይሄዳሉን?» እርግጥ ነው አንድ እርምጃም፣ መራመድ አይችሉም። እንዲህ ዓይነት ሕይወት፣ ለጌታም ለሰውም አስቸጋሪ ነው። በረከት የለበትም።

ዘጠኝ

የእግዚአብሔር ቃል እየደጋገመ የሚያስተምረን፣ ስለ አንድነ ት/መዋሃድ/ አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ነው። ለመዋሃድ ደግሞ ቁል ፍ የሆኑት ነገሮች፣ የሚከተሉት ናቸው።

1. በመጀመሪያ ሰው ራሱን መቀበልና መውደድ መቻል አለበ ት። ምክንያቱም ራስን መወንጀልና የበታችነት ስሜት፣ ለጤ ናማ ትዳር ትልቅ ጠርና መሰናክል ነው።
2. አንድ ሰው ከሌላው ጋር ለመጣበቅ ከመሞከሩ በፊት፣ ከራሱ ጋር መዋሃድና መጣበቅ መቻል ይገባዋል። ምክንያቱም ችግር ያለበት ሰው ሁልጊዜ ከራሱ ጋር ይጣላልና ነው።
3. ለራስ አስተሳሰብና ፍላጐት፣ ሙሉ በሙሉ መሞት። ማለትም የሌላውን መብትና ደካማ ጎን፣ አምኖ መቀበልና ለሌላው ለ መኖር መወሰን።

4. የሚጣበቀውን ስው፣ ከጌታ የተቀበለው ብቸኛ ስጦታ መሆኑ ን፣ አምኖ መቀበልና፣ ስጦታውን በጥንቃቄ መጠበቅ:: ዋና ዋ ናዎቹ ናቸው::

ልብ በሉ:- ሰው ከራሱ ጋር መዋሃድ ካልቻለ፣ ሙሉ ሰው መሆኑ ያጠራጥራል:: ባልና ሚስት አንድ ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም:: ይህንን እውነት፣ የሚከተሉትን የእብራይስጥ ቃላቶች በመውሰድ፣ እንመልከታቸው::

ባልና ሚስት፣ ሁለቱም አንድ ሥጋ ናቸው

- **ኤሃድ** /One/ የሚለው የእብራይስጥ ቃል የሚያመለክተው፣ ሁለት የተለያየ አካል ያላቸው አንድ አካል ሲሆኑ ነው:: እንደገናም በእብራይስጥ፣ ኢሽ ወንድ ሲሆን ኢሻ ደግሞ ሴት ማለት ነው:: ሁለቱ በአንድነት ሲጠሩ፣ አናሽም ይባላሉ:: ስለዚህ ከዚህ አሳብ ተነስተን፣ ባልና ሚስትን ስናያቸው፣

  1. ሁለት የተለያዩ ባለ ታሪኮች፣ ቃል ኪዳን በሚባል ማጣበ ቂያ መሣሪያ፣ አንድ ታሪክ ሆኑ፣ የተለያየው ቅርጻቸው በአንድ ተጋጠመ ማለት ነው::
  2. የአዳም አጥንት መልኳን ቀይራ፣ ሔዋን ውስጥ ገባችና ተ ቀላቀለች፣ ለማለት ነው:: ያም በግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው:: ይህን በሚቀጥለው ምዕራፍ በስፊው እናየዋለን::
  3. ባልና ሚስት፣ የአንድ የሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው::

- **ሁለቱም ራቁታቸውን ነበሩ**

  አራሚም/Naked/ 1. ራቁት ምንም ነገር ያልለበሰ
  2. ግልጽ የተደበቀ ነገር የሌለበት
  3. እውነት ምንም ነገር ያልተጨመረበት

4. የሥጋ ራቁትነት /የግብረ ሥጋ ነጻነት/
5. የውስጥ የመንፈስና የነፍስ ግልጽነት
6. የተጋለጠ ሕይወት

አይተፋፈሩም ነበር፣ ሚትባየሽም /Ashamed/ መተፋፈር ማለት ሲሆን፣ እዚህ ላይ ግን አይተፋፈሩም ነበር፣ ነው የሚለው:: ማለትም:-


1. የጽድቅን ሕይወት መኖር
2. መደነጋገር የሌለበት ሕይወት
3. የነሲና ክስ የሌለበት
4. ያልተታለለና ያልተጭበበረ ሕይወት
5. ጠባሳ ነገር የሌለበት ማለቱ ነው::

ስለዚህ ጋብቻ ከላይ ባሉት የአብራይስጥ ቃላቶች ሲተነተን:-

- የሁለት ባለታሪኮች የታሪክ ስብስብ ነው
- ከማንም ምንም የማይፈልግ፣ ራሱን ችሎ የቆመ፣ በጥቅም ያልተመሠረተ ሕይወት ነው::
- የያሕቄ አውነትና የነጻነት መብቀያ ነው:: ዮሐ. 8:32
- የበረከት መፍለቂያ ምንጭ ነው
- ኮንትራት ያልሆነ መጨረሻ የሌለው ቃል ኪዳንና፣ የሕይወት ውል ነው:: ዘፍ. 22:16
- የእርካታና የዕረፍት ቦታ ነው::

የጋብቻ ምሳሌ በስሳሌ ባህሬ ውስጥ ይገኛል

ዘፍ. 1:27፣ ዘፍ. 2:24፣ መኃ. 4:9-12



ጌታችን እየሱስ /የሹአ/፣ እየደጋገመ፣ ይህን እውነት በቃሉ አስረግጦ አስረድቷል። ማቴ. 19:5-6

«ስለዚህ ሰው አባትና እናቱን ይተዋል፣ ከሚስቱም ጋር ይተ ባበራል፣ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነ በባችሁምን? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለ ት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አ ይለየው።» ይላል። በተጨማሪም ዘፍ. 2:24፣ ኤፌ. 5:31

«ፍቅር» ባለበት ውጎደት አለ። ሐዋርያው ጳውሎስ በቆላ. 3:14 ላይ እንዲህ ይላል።

> «በእነዚህ ሁሉ ላይ የፍጻሜ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት፣ በአንድ አካልም የተጠራችሁለት ደግሞ የክርስቶስ ሰላም/ሻሎም/ በልባችሁ ይግዛ፣ የምታመሰግኑም ሁኑ።»

ፍቅር ሁልጊዜ ይለበሳል። እንደ ጨርቅ የሚያረጅ ነገር አይ ደለም። ይልቁንም በየቀኑ፣ እየታደሰና እየጣፊጠ ይሄዳል። የጌታ እየሱስ /የሹአ/ አጋፔ ፍቅር ባህሪው ይኸው ነው። «ትዳርና ጫማ እያደር ይመቻል» የሚለውንም አባባል ብንጨምርበት፣ አሳባችንን ያጎለምስልናል፣ ብዬ እገምታለሁ።

ሌላው ለመዋህድ ቁልፍ የሆነው መፍትሔ ደግሞ፣ «ይቅር» መባባል ነው። ሰው ፍጹም አይደለም። እያንዳንዱ ግለሰብ ይብዛም ይነስም፣ የራሱ የሆነ ጐዶሎ ነገር አለው። ፍጹምና እንከን የሌለበት ጌታ ብቻ ነው። መላዕክት፣ ፀሐይና ጨረቃ እንኳ በእግዚአብሔር ፊት ፍጹሞች አይደሉም። ስለዚህ የትዳር ጓደኛህ/ሽ/ ፍጹም አይደለም/ለችም/። ወደ ፍጹምነት በሚወስደው ጎስሐ፣ ሁልጊዜ ከ ልብ ይቅር መባባል ተገቢ ነው። ፍቅር ሁልጊዜ በደልን አይቆጥ ርም። ፍጹም ይረሳል። ይተዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ያረጋግጥ ልናል።

> «ፊተኛ ኑሯችሁን እያሰባችሁ እንደሚታለል ምኞት የሚጠ ፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ። በአዕምሯችሁም መንፈስ ታደሱ ለእውነትም በሚሆን ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአ ብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን ሰው ልበሱት።»
>
> ኤፌ. 4:22-24

> «እርስ በርሳችሁ ቸሮችና ሩኅሩሆች ሁኑ እግዚአብሔር ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ።»
>
> ኤፌ. 4:32

«እናንተ ግን ይቅር ባትሉ በሰማያት ያለው አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።» ማር. 11:26 ይላል።

ቃሉ እውነተኛና የታመነ በመሆኑ፣ የሚለውን ማድረግ ተገቢ ነው። ይቅር ካላልክ አትቀበልም። ብዙ ሌላ የሂሳብ ስሌት ለዚህ አያስፈልግህም። ለመፈወስ ከፈለግህ ከልብህ ይቅርታን ስጥ። እንዲህም ተቀበል። «ፍቅር በደልን አይቆጥርም።» 1ኛ ቆሮ. 13:5 ይህን ሁልጊዜ አስብ። «ጆሮ ያለው ይስማ።»

ለመዋህድ ሦስተኛው ነጥብ ደግሞ፣ «ውሸትን ማስወገድ /እውነተኛ መሆን/ ነው። የህሰት መነሻና መድረሻው፣ ሰይጣን ነው። ጌታ እየሱስ /የሹአ/፣ ክፉውን እንዲህ በማለት ይገልጸዋል።

«እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ /ሰይጣን/ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበር፣ እውነትም በእርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል። ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና።» ዮሐ. 8:44

የውሸት መንፈስ የሚያስቸግረው ሰው፣ መንፈሱን በእየሱስ ስም ገስጾ ማውጣት ያስፈልገዋል። በማመቻመች ደብቆ ይዞ፣ በመንፈሱ ውስጥ ማሳደግ አይገባውም። ውሸት ትልቅ ኃጢአት ነው። ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይመክራል።

«ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነና ልና አያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ።» ኤፌ. 4:25

እንግዲህ እስኪ እናንተው ፍረዱት። ከባልና ሚስት የበለጠ አንድ አካል ወዴት ይገኛል? ባልና ሚስት እርስ በእርሳቸው የሚዋሻሹ ከሆነ፣ እውነተኛ ትዳር ውስጥ እንዳልሆኑ ይረዱት። ምክን ያቱም ራሳቸውን እያሳቱና እያታለሉ ነውና። የእግዚአብሔር ቃል

ውሸትን አስወግዱ፣ ጥሉት፣ ተጸየፉት ነው የሚለው:: ስለዚ ህ ባልና ሚስት፣ እባካችሁ እውነትን እርስ በእርሳችሁ ተነጋገሩ::

እውነት ነጻ ያወጣል:: የፈለገውን ያህል ውሸት ቢበዛ፣ አንድ ቀን ትንሿ እውነት ትደመስሰዋለች:: «ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል::» የሚለውን ከንቱ ፍልስፍና፣ መቀበል እያስፈልግም:: ጌታችን ሁልጊዜ ከእውነት ጋር እንድንቆም ነው ያስተማረን:: ስለ ዚህ የእርሱን ፈለግ በመከተል፣ መገስገስ ተገቢ ነው:: ከመጽሐፈ ምሳሌ ተጨማሪ ምክሮችን ልጨምርበት::

ምሳሌ 24:3-4 «<u>ቤት በጥበብ</u> ይሰራል <u>በማስተዋልም</u> ይጸናል <u>በእውቀት ከከበረውና ካማረው ሁሉ</u> ንዳዎች ይሞላሉ::»

ምሳሌ 15:33 «እግዚአብሔርን <u>መፍራት የጥበብ</u> ትምህርት ነው:: <u>ትህት ናም ክብርን</u> ትቀድማለች::»

ምሳሌ 18:1 «<u>መለየትን</u> የሚወድ <u>ምኞቱን ይከተላል</u> መልካሙንም ጥበብ ሁሉ ይቃወማል::»

ምሳሌ 1:33 «የሚሰማኝ ግን በእርጋታ ይቀመጣል ከመከራም ስጋት ያርፋል::»

ምሳሌ 16:7 «<u>የሰው አካሄድ</u> እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘው እንደሆነ በእርሱና በጠላቶቹ <u>መካከል</u> ሰላምን ያደርጋል::»

ምሳሌ 13:10 «<u>በትዕቢት</u> ጠብ ብቻ ይሆናል:: <u>ጥበብ ግን ምክርን</u> በሚቀበሉ ዘንድ ናት::»

በመጨረሻም ሰባል ይህን ምክር እመክራለሁ:-

ኤፌ. 5:33 «ሆኖም ከእናንተ ደግሞ <u>እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን</u> እን ዲህ እንደ ራሱ አድርጐ <u>ይወደዳት፣ ሚስቱም ባሏን ትፍ ራው::</u>»

ከዚህ ቀደም እንዳልኩት፣ የሚስትህን ሙያና ውበት አድንቅ ላት:: መውደድህንም በቃላትና በተግባር ግለጽላት:: የምትጠነቀ ቅላት መሆንህን የምታውቅበትን መንገድ ቀይስላት :: በማቀፍና በ መቀላለድ ጨዋታ፣ ከሚስትህ ጋር ያለህን ግንኙነት ጤናማ አንዲ ሆን መንገድ ክፈትላት:: ልብ በል! ሚስትህ አካልህ ናት:: እርሷን ከሁሉም በፊት ልትወዳትና ልታከብራት፣ አድናቆትህንም ልትገል ጽላት ይገባል::

«በሰው ወርቅ አያጌጡምና» የሌላውን ሚስት ማድነቅህ፣ ላንተ ምንም አይጨምርልህም:: እንዲያውም ከሚስትህ ጋር ያቃር ንሃል:: ያራርቅሃል:: ሌላም ልጨምርልህ «በሚስትህ ፊት፣ በፍጹም የሌላ ሰው ሚስት አታድንቅ::» ይልቁንም የራስህን ሚስት የቤት አያያዟን፣ የሰራችውን ምግብ፣ የልጆች አስተዳደጓን፣ ፈገግታዋን፣ ትህትናዋን አድንቅላት:: ሌላው ቀርቶ አለባበሷንና አረማመዷን አወድስላት:: እንዲህ አይነቱ ልምድ፣ የሚስትህን ልብ እንደ ሰም ከማቅለጡም በላይ፣ መልካም ምግብና የጣፈጠ መኝታ፣ አንድታገኝ ያደርግልሃል::

ለሚስት ደግሞ ያለኝ ምክር:-

ባልሽን በፈሪሃ እግዚአብሔር መንገድ አክብሪው:: የፍቅር ፍ ርህት ለባል ያስፈልገዋል:: «ባለቤቱ የናቀውን አሞሌ/ጨው/፣ ባለዕ ዳ አይቀበለውም» ሲባል አልሰማሽም? የራስሽን ባል እያናናቅሽ የሌላውን ብታከብሪ፣ የሚሰሙሽ ሁሉ ሞኝ ይሉሻል:: ባል የጌታ ምሳሌ ነው:: ቀድሞም የተፈጠረው እርሱ ነው:: የባልሽን አቅ ጣጫ ለማስቀየር፣ ቁልፉ በእጅሽ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚ ለው ብትራመጂ፣ በሕይወትሽና በትዳርሽ ትረኪያለሽ:: ክብርን ለሚገባው ክብርን ስጡ፣ ይላልና:: በምድር ካሉ ሰዎች፣ አብልጠሽ ልታከብሪውና ልትጠነቀቂለት የሚገባው ባልሽ መሆኑን፣ አበክረሽ እወቂ::

እንግዲህ እነዚህ ለመዋህድ ዋና ዋና ቁልፎች በመሆናቸው፣ ባልና ሚስት ድርሻቸውን በትጋት ሊፈጽሙ ይገባቸዋል። በተግባር ከተተረጐሙ፤ ትልቅ የትዳር ለውጥ ያመጣሉ። ባጠቃላይ ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸውን አሳቦች፣ ተጠቀሙባቸው። ሳትተዋወቁ ዘመና ችሁን በከንቱ አትጨርሱ። ዛሬ የመታደስና የመቀየር ቀን ይሁን ላችሁ። ጌታ አየሱስ አሮጌውን የትዳር እርሾ በማስወገድ፣ አዲስ ምዕራፍ በሕይወታችሁ መክፈት እንደሚችል እመኑት። «በዙፋኑ የተቀመጠው፣ እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ።» አሜን። ራዕይ 21፣5



ስትከላከሉ!

አትከላከሉ በሚለው ርዕስ ሥር፣ ሁለት በጣም ጠቃሚ የሆኑ ክፍሎችን እናጠናለን። እነርሱም፡- የትዳር ቅመምና ግብረ ሥጋ ግንኙነት በረከት ነው፣ የሚሉት ናቸው። እነዚህ ክፍሎች የትዳርን እርምጃ ለማፋጠንም ሆነ ለማዘግየት፣ ቁልፍ መንገዶች ናቸው። ስ ለዚህ ባልና ሚስት በጥንቃቄ እየተደጋገሙ እንዲያነቧቸው አደፋፍ ራለሁ።

6-1. የትዳር ቅመም

ታሲተስ /Tacitus/ የተባለ ላቲናዊ አባት «ራስ መዳድነት ለእውነተኛው ነገር ሁሉ ጠላት ነው» አለ። ምናልባት ብዙዎቻችሁ ምን ይሆን የትዳር ቅመም? ልትሉ ትችላላችሁ። መልሱን እየቆየን እንመጣበታለን።

ብዙ ጊዜ በኢትዮጵያውያን ተጋቢዎች ዘንድ፣ ግልጽ ውይይ ት የማይደረግበት፣ <u>ትልቁና ያሳፍራል ተብሎ የሚገመተው ጉዳይ ቢኖር፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው</u>። እርግጥ ነው የግብረ ሥጋ ግ ንኙነት፣ አስቸጋሪ ነጥብ ስለሆነ፤ ለመወያየትና በቀላሉ መፍትሄ ለመስጠት ያዳግታል። ይልቁንም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ፣ የባሕል ተ ጽዕኖ ከፍተኛ በሆነባቸው አገሮች። ይሁንና ሕብረተሰቡ ሊያሻሽ ለውና ሊለምደው የሚገባ፤ ትልቅ የጋብቻ መሠረትና የሕይወት ቁ ልፍ ነው።

የግብረ ሥጋ አለመጣጣም፤ በሰው ሕይወት ውስጥ የስሜት ችግርና ጫና የመፍጠር ኃይል አለው። ከዚያም ባሻገር ትዳርን

በማቀጨጭ፣ የተዛባ ሕብረተሰብ እንዲፈጠር ያደርጋል። የግብረ ሥጋን አስደሳች ጣዕም ለመለማመድና ለዘለቄታ በውስጡ ለመኖር፣ የሚያስችሉ አራት መሰረታዊ የመገናኛ ወይም የመወያያ ነጥቦችን ከዶ/ር ዶግላስ ሮዝኑ መጽሐፍ የወሰድኩትን አሳብ ከዚህ በታች አስፍሬዋለሁ።

እንደ ጸሐፊው አገላለጽ፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት፣ ለባልና ሚስት የየቀን የተግባር አንድነት፣ ወሳኝ አይደለም ይላሉ። ይልቁንም፡- ለትዳራቸው መስመርና የተጣመረ ሕይወት ቁልፉ፣ እርስ በእርሳቸው የሚወያዩትና፣ በንግግራቸው የሚፈጥሩት የፍቅር አየር ነው። በማለት ውይይትን በትልቁ ያስምሩበታል። ባልና ሚስት የሚቀላለጿቸውና የሚላኩቸው ሁኔታዎች፣ ይልቁን ለትዳር መዋሀድ፣ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው።ይሉና፡- ከዚህ በታች ያሰፈርኳቸውን አራቱን ነጥቦች ይገልጹልናል።

ማሳሰቢያ፡- ከዚህ በታች በወንድ ፆታ ብቻ የተጻፉት፣ ለአጻጻፍ እንዲመች ታስቦ ስለሆነ፣ ሴቶችም እንደፆታችሁ እንድታነቡት አደራ ፋፍራችኋለሁ።

ሀ- በነቃና በተከፈተ ጆሮ የትዳር ጓደኛን ማዳመጥ፡

እንደ ጸሐፊው አገላለጽ፣ ማንኛውንም ቃልና ዓረፍተ ነገር፣ በጥንቃቄ ማዳመጥ፣ ከሁሉ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው ይላሉ። እንደገናም በዓይን ትክ ብሎ እየተያዩ፣ በትዕግስት የተናጋሪውን አሳብ ማስጨረስ፣ ሌላው ትልቅ ቁም ነገር ነው። መስማት ሳይሆን ማዳመጥ። ሁለቱ ትልቅ ልዩነት አላቸውና። በውይይት የማትስማሙበት ነጥብ ቢኖር፣ ቶሎ ብሎ ሳይፈርዱና ውሳኔ ሳይሰጡ፣ ምናልባት የእኔ አሳብ ልክ ባይሆንስ? ብሎ በተለያዩ አቅጣጫዎች፣ ጥቅሙንና ጉዳቱን መመርመር። እንዲህ አይነቱ ልምድ በቀላሉ ወደ መፍትሄ ለመምጣት ያስችላል። በነገራችን ላይ ዓይን ለዓይን መተያየት፣ ትልቅ ኃይል አለው። ስለዚህ ባሕላችን ትሕትና ነው

ብሎ ያስተማረንን፣ አንገት መድፋት በማቆም፣ ቀና ብለን መናገር ን እንድናሻሽል፣ ምክሬን አለግሳለሁ።

ለ- የሚሰማህን ሁሉ ሳትደብቅ ግልጽ በሆነ መንገድ ማስረዳት፡

የትዳር ጓደኛህን ስሜት ሳትጎዳ፣ በታላቅ ጥንቃቄ አስፈላጊ ውን መልእክት፣ በቀና መንገድ አስተላልፍ። በቃል የተጎዳን ስሜ ት መጠገኑ ከባድ መሆኑን አስቀድመህ እወቅ። በቃል ለቆሰለ ሰው፣ በቀላሉ ፈውስ አይገኝለትም። ስለዚህ ለስሜትህ ልዩ ትኩረ ት በመስጠት፣ አሳብህን በማስተዋል መግለጽ ተለማመድ። አስታ ወስ ጤናማ ትዳርና ፍቅር የሚወለደው፣ ከአንደበትህ ነው።

ሐ- ማስተላለፍ የፈለከውን ትክክለኛውን መልዕክት እወቅ፡

ዋና ዋና ነጥብህን በቀጥታና ግልጽ በሆነ መንገድ አስረዳ። ለ ማንኛውም ለምታቀርበው አሳብ፣ ተቃውሞና የአሳብ ልዩነት የሚያ መጣ መስሎ ከታየህ፣ አስቀድመህ ራስህን ለሚመጣው ችግር አዘጋ ጅ። የአኔን አሳብ ካልተቀበልሽ የፈለግሽውን ሁኝ፣ በማለት የአካል ህን መብት እንዳትነፍግ ተጠንቀቅ። የአሳብ ልዩነቱ ያሳድጋችኋል እንጅ፣ የሚጎዳችሁ እንዳልሆነ ተረዳ። ያ ባየሆን ኖሮ፣ አግዚአብሔ ር ወንድና ሴት አድርጎ መፍጠር ባላስፈለገውም ነበር። ቶሎ ቶሎ ቱግ እያሉ አራስ ነብር መሆኑ፣ በቤት ላይ ክብሪት ከመጫር በስተቀር፣ የሚፈይደው ጥቅም እንደሌለው ተገንዘብ። ስለዚህ በትዕ ግስት ስሜትህን በመግታት፣ ነጥብህን አስረዳ።

መ- የአሳብ መለያየት ቢኖር፣ ግንኙነትህን አጎልብተው እንጅ እትግታው፡-

ብዙ ሰዎች ከትዳር ጓደኛቸው ጋር የአሳብ ልዩነት እየተደጋ ገመ ሲፈጠር፣ በቀላሉ ተስፋ ስለሚቆርጡ፣ አሳባቸውን ለራሳቸው አምቀው በመያዝ ለጭንቀት ይዳረጋሉ። የእነዚህ አይነት ሰዎች ችግር፣ በአንተም ላይ እንዳይደርስ፣ በማንኛውም ነገር በቶሎ ተስፋ

አትቁረጥ። ስለዚህ ምንም ይሁን ምን፣ ሁልጊዜ በተለያየ መንገድ ለትዳር ጓደኛህ የሚሰማህን ሁሉ ሳትደብቅ፣ ግልጽና አጭር በሆነ እረፍተ ነገር መግለጽህን ቀጥል። በትንሹም በትልቁም ነገር እታኩ ርፍ። ብዙ በመናገር ብዙ ከንቱ ነገር አለና ፍሬ ነገሩን ብቻ በአጭር ለማስጨበጥ ሞክር። ሰሚህ ቁም ነገሩን መጨበጧን ለማወቅ ደግሞ፣ አሳቧን እንድትገልጽ ጊዜ ስጣት።

ከላይ የጠቀስናቸው አራት ነጥቦች፣ ለሩካቤ ሥጋ መቃናት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ለግብረ ሥጋ ግንኙነት መስመርና መጣጣም ሁልጊዜ ወሳኙ አንተው ነህ እንጅ፣ ጓደኛህ ብቻ አይደለችም። ከሚስትህ ጋር ብዙ ባወራህና በተሻሸህ፣ በተሳሳምክና አብረህ በወጣህ ቁጥር፣ ፍቅርን እንደ ውኃ ፈሳሽ እያበዛህ መሄድህን ተረዳ።

በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ፣ ለሩካቤ ሥጋ የሚያነሳሳ ቀልድና ጨዋታ ለሚስትህ ጣል ማድረጉ፣ ይበልጥ እርሷን ያዘጋጃታል። እንዲህ ዓይነቱ ልምድ፣ ከሚስትህ ጋር ያለህን የወሲብ ፍላጎትና ጣዕም እድሜውን ያራዝምልሃል። ስለዚህ ተግተህ አድርገው። ይህን ስል ግን ጊዜና ሁኔታን ተጠቀም እንጅ፣ በየሰው ፊትና የጸሎት ቦታው፣ ሌት ከቀን እርሱን አስብ ማለቴ አይደለም። ጥበበኛው ሰሎሞን ለሁሉም ጊዜ እለው፣ ያለውን ድንቅ ቃል ተመራበት።

ከትዳር ጓደኛህ ጋር በየቀኑ መቀላለድ ኃጢያት አይደለም። ቃልህ ነው የሚስትህን ስሜት የሚቀሰቅስልህና፣ ራሷን ለእንተ አሳልፋ እንድትሰጥ የሚያደርጋት። የሩካቤ ሥጋን አስደሳች የሚያደርገው፣ ከጨዋታና ቀልድ ጋር ሲከናወን እንደሆነ የጋብቻ ጠበብት ይናገራሉ። ምንም እንኳ ዋዛና ፈዛዛ አስፈላጊዎች ባየሆኑም፣ በባልና ሚስት መካከል የሚደረጉት ለዛ ያላቸው ቀልዶች፣ ስሜትን ለማፍታታትና ለመኝታ ለመዘጋጀት፣ መንገድ ጠራጊዎች ናቸው።

ሁልጊዜ ግንባሩን አኮሳትሮ ጀግና ነኝ እያለ የሚታበይ ባል፣ ስለ ሚስቱም እርካታና ደስታ ደንታ የሌለው ነው። ሴትን መጠቀ ሚያ ዕቃ እድርጎ የሚያስብ ነው። አስታውስ፡- ለሚስትህ ራስህን ቀለል በማድረግ እንደ ጓደኛ ካልቀረብካት፣ በፍርሃት ስለምትዋጥ፣ ለግብረ ሥጋ ግንኙነት ያላትን ፍላጎት ትዘጋባታለህ። ስለዚህ በተቻለህ መጠን አንተነትህን፣ ሙሉ በሙሉ እንድትደሰትበት ሁኔ ታዎችን አመቻችላት። ልብ በል ወንድሜ፣ ሚስትህ አካልህ ናት እንጂ፣ ጉብዝናህን የምትፈትንባት ባላንጣህ አይደለችም።

በአማኞች ላይ አይብዛ እንጅ፣ በአብዛኛው የአገራችን ክፍ ሎች ሴት በብዙ ምሬትና ጭንቀት የምትኖረው፣ የመናገርና የመ ደመጥ መብት ስለተነፈጋት ነው። ከዚያም አልፎ፣ ለመኝታ ተገዳ ም ይሁን ወዳ ስትሄድ፣ የወሲብ ፍላጎቷ በተገቢው መንገድ ስላልተ ነቃቃ፣ የጭንቀት መንፈስ እንዲፈጠርባት ትሆናለች። ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ አጥታ ስለምታድር፣ ቀኑን ያነጫንጫታል። የበሽታ ው መነሻ እርሱው እንደሆነ ያላወቀው ወንድ፣ ጤና ጎድሏታል በማለት ወደ ፍች ያመራል።

ወይም ሌላ ሴት በመያዝ የተለያዩ ልጆችን ይወልዳል። እንደዚህ የሚወለዱት ልጆች ደግሞ፣ ሳይሳካላቸው ባልተመጣጠነ የአባትና እናት ፍቅር ስለሚያድጉ፣ ለምድሪቱ በረከት በመሆን ፈንታ፣ ሸክሞች ይሆናሉ። በተለያዩ ወንጀሎች በመሰማራት፣ ሕብረ ተሰቡን ያውካሉ። በዚህ ምክንያት አገር እየወደቀችና እየወደመች ትሄዳለች። አገሪቱ የለማኝና የበሽታ መናህሪያ በመሆን፣ የወላድ መካን ሆና ስታለቅስና ስትጠቃ ትኖራለች።

እንግዲህ ይህን አሳብ ላመጣው ያሰገደደኝ፣ በገጠርና በከተማ ከሚታየው የትዳር መናጋት በመነሳት እንጅ፣ ዳግም የተወለዱትን ለማለት አይደለም። ይሁን እንጅ ከጥቂት አመታት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ምእመናንም ዘንድ እንዲህ አይነት ስሞታ መሰማት እየ ተለመደ ስለመጣ፣ ሥር ሳይሰድ እንዲቀጭ የቤተ ክርስቲያን መሪ

ዎች ጠንከር ያለ አቋምን መውሰድ ቢጀምሩ፤ መልካም ነው በማ ለት ያለኝን ምክር አለግሳለሁ።

ታላላቅ አፍቃሪዎች የሚባሉት፤ ኃይላቸውንና ጊዜያቸውን አሰባስበው፤ የጓደኞቸውን የግብረ ሥጋ ፍላጎት ለማርካት፤ የሚችሉ ናቸው። ዶ/ር ዱግለስ ሮዝኑ የሩካቤ ሥጋ አለመጣጣም የሚየስከ ትለውን ቀውስ ሲናገሩ እንዲህ ይላሉ፡-

"የሩካቤ ሥጋ አለመጣጣም፤ ዋና ዋና የሚባሉ የጤና ቀው ሶቸን ያስከትላል። ከእነርሱም ውስጥ ጭንቀት፣ ፍርሃት፣ የበደለ ኛነት ስሜት፣ ብስጭት፣ ንቀትን፣ ተስፋ መቁረጥን፣ አለመተማ መንንና፣ ቅናትን ይፈጥራል። በማለት ሲያስጠነቅቁ፤ በአንጻሩ ደግ ሞ የሩካቤ ሥጋ መጣጣም፤ የልብ ፈውስን፣ መርካትን፣ መተማ መንን፣ መተሳሰብን፣ እውነተኛ ዕረፍትንና ሰላምን ያመጣል" በማለ ት ያስገነዝባሉ።

ምናልባት አርሳቸው እንዳሉት፤ የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ የልብ ቁስልና የጨጓራ በሽታ መነሻው፤ በጋብቻ ውስጥ ካለመርካት ና ከሩ ካቤ ሥጋ አለመጣጣም የሚመጣ ነው ብል፤ የተሳሳትኩ አይመስለኝም። በእርግጥ መነሻው ይህ ከሆነ ደግሞ፤ መድኃኒቱ የ ሚገኘው፤ በሆስፒታል ሳይሆን፤ ባልና ሚስት በየቀኑ ከሚያደርጉት የፍቅር እርካታና ውይይት ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችንም ከዚህ አሳብ ጋር በ መስማማት

> «እንደ ተወደደች ዋላ እንደ ተዋበችም ሚዳቋ፤ ጡትዋ ሁል ጊዜ ታርካህ፤ በፍቅርዋም ሁልጊዜ ጥገብ» ይለናል።
>
> ምሳ. 5፣19

አድሜ ማስቆጠሩና ልጅ መውለዱ ብቻ፤ የትዳርን መቃናት አያሳይም። በትዳራቸው መብሰላቸውና መጣበቃቸው ከሚታወቅባቸ ው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ፤ የመኝታቸውን ችግር በግልጽ መወያ የት መቻላቸውና መፍትሄ ማግኘታቸው ነው። የእውነተኛ ፍቅር

መለኪያው ራቁትነት በመሆኑ፤ ግልፅነት የትዳሩ ምሰሶ ሊሆን ይገ ባዋል::

አንድ ጊዜ የጋብቻ ሴሚናር ስሰጥ፤ በብጣሽ ወረቀት የመ ጣውን ጥያቄ በፍጹም አልረሳውም:: አሳቡን የጻፈችው፤ ስሟን ያል ገለጸች በሩካቤ ሥጋ አለመጣጣም የታወከችና በባሏ ራስ ወዳድነት የተማረረች እህት ናት:: የሚለውም አንዲህ ነው:- <u>ፓስተር አንተ በግልጽ ችግሮችን እንደ ምታስተምር አይቻለሁና፤ እባክህ ለወንዶች የሩካቤ ሥጋ በኃይል እንደማይደረግ አስረዳልን፤</u> የሚል ነበር:: ጥያ ቄው ከአንድ ሴት ይምጣ እንጅ፤ የአብዛኛዎቹ ሴቶች የልብ ቁስል መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው::

ወንዶችስ ይህን ጥያቄ እንዴት ትመለከቱታላችሁ? ወገኖቼ መቸም የሩካቤ ሥጋ የኃይል ማሳያና የጉልበት መፈተኛ ሳይሆን፤ የፍቅርና የደስታ መፍለቂያ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱሳችን በግልጽ ያስረዳናል:: የሩካቤ ሥጋ የራሱ ሕግና ደንብ አለው:: የእጠቃቀሙ ን ስልት መማሩ በጣም አስፈላጊ ነው:: በመጀመሪያ እግዚአብሔር የሩካቤ ሥጋን ለክብሩ መግልጫ ለሆነው ሰው ሲሰጠው፤ እንዲደስ ትበትና ዘርን እንዲተካበት ነው:: ማለትም ወንድም ሆነ ሴት፤ የ መደሰትና የመርካት መብት አላቸው:: አንዱ ተደሳች፤ ሌላው ክፍ ል አዛኝና ቆዛሚ እንዲሆንበት እግዚአብሔር አልፈቀደም:: የሩካቤ ሥጋ በቤት ውስጥ ለሚፈጠረው ሰላም ትልቅ አስተዋፅዖ አለው::

ባል:- አጥብቀህ ልትረዳው የሚያስፈልግ ጉዳይ ቢኖር፤ ያገባ ሀት ሴት ስጦታህ መሆኗን ነው:: ስለዚህ በቀስታ መምራት እንጅ፤ በኃይል ተጭኖ ማድቀቅ ተገቢ አይደለም:: እርግጥ ነው የፍትወት ጉዳይ፤ ትዕግስት የማይሰጥበትና ከቁጥጥር በላይ የሚሆንበት ጊዜ አለ:: ይሁን እንጂ ራስን የመግዛት መንፈስ ደግሞ፤ የመንፈስ ፍሬ መሆኑን መርሳት አይገባም:: የሩካቤ ሥጋ ብዙ እወያይና በቃላት ብቻ የማይገለጽ ሰፊ ከፍል በመሆኑ፤ በተቻለኝ መጠን፤ ችግሮችንና

መፍትሄዎችን በመዘርዘር፤ ለአዲስ ተጋቢዎችና ለመጭው ትውልድ ለማስተላለፍ አጥራለሁ።

አዲሱ ትውልድ ለመሻሻልና ለማደግ፤ የዕውቀት አድማሱን ሰፋ በማድረግ፤ በማንኛውም አቅጣጫ ለተሻለ ሕይወት መነሳት ያስ ፈልገዋል። በተለይ አዳዲስ ግንኙነቶችን ለመቀበልና በምድሪቱ ላይ ለውጥ ለማምጣት በኢያሱ መንፈስ መታጠቅ ይጠበቅበታል። ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የአባቶቻችን ወግና ባሕል፤ እንዲሁም ኃይማኖት እያሉ፤ እርምጃን ከሚያደናቅፉ አጉል ልምዶች ነጻ መ ውጣት ያስፈልገዋል።

እርግጥ ነው ከአባቶቻችን የምንወስዳቸው፤ ብዙ ጠቃሚ ባሕ ሎች አሉን። ይሁን እንጅ ትዳርንና የሩካቤ ሥጋ እጠቃቀምን፤ ከባ ሕላችን ብቻ መውረስ በቂ መስሎ አይታየኝም። የሙሴንና የእያ ሱን ትውልድ ስንመለከት፤ ያለፉበትና የተጓዙበት መንገድና ዘዴ አንድ ዓይነት እንዳልነበረ፤ መጽሐፍ ቅዱሳችን በግልጽ ያስተምረ ናል። በዘመናችን ማድረግ ያለብን ይህንኑ ዓይነት ለውጥ መፈለግ ነው። የተገለጠልንን የጊዜውን እውቀት ሸምተን፤ ለመጭው ትውል ድ ብናስተላልፍ፤ በትዳራቸው እንዲደሰቱ፤ በር መክፈታችን መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

በሌላ በኩል ደግሞ፤ በሰለጠነው አገር እየኖሩ፤ ሚስቴንና ልጆ ቼን እንደ አገሬ ባሕልና ወግ ነው የማስተዳድረውና የምመራው ማለቱ፤ ሞኝነት ነው። ምክንያቱም የምዕራቡ ዓለም አስተዳደር ሚስትንም ሆነ ልጅን መብታቸው እንዲነካ አይፈቅድምና ነው። የምርጫም ጉዳይ ሳይሆን የግዴታ ሊጠበቅና ሊከበር የሚገባው ህግ ነው። ይህን ህግ መጣስ በቤተ-ሰብና በማህበረ-ሰብ ላይ ኪሣራ ማስ ከተሉ ብቻ ሳይሆን፤ በህግ ያስቀጣል።

እንግዲህ የግብረ ሥጋ ግንኙነት፤ ዋናው የጋብቻ ማጣፈጫ ቅ መምና አነቀሳቃሽ ሞተር መሆኑን፣ ከሁሉም በላይ መግንዘብ አስፈ

ላጊ ነው። ይህንን ሞተር ለማንቀሳቀስ የልብንና የመንፈስን መስኩ ት በመክፈት፤ በእንደበት መታወጅ አለበት። አርግጥ ነው ባሕላ ችን የሩካቤን ሥጋ ጭውውት፤ ነውር አድርጎ ነው ያስተማረን። የአግዚአብሔር ቃል ግን አዳምና ሔዋን ራቁታቸውን ነበሩ አይተ ፋፈሩም ነበር በማለት ያሰምርበታል። ታዲያ ቃሉ እንዲህ ከሆነ የሚለው፤ መተፋፈርና መሸፋፈን ከየት መጣ? ሰይጣን መልካም አስመስሎ በባሕል ሰበብ ቤተሰብን ለማወክ የሚጠቀምበት መሳሪያ ው እንደሆነ፤ መርሳት አይገባንም።

በዚህ "አትከላከሉ" በሚለው ዋናው ዕርሳችን ሥር፤ በግልጽ ማተኮር የፈለኩት ጉዳይ ቢኖር፤ በባልና ሚስት መካከል የሩካቤ ሥጋ አሳፋሪ አለመሆኑን ነው። ስለሆነም ባልና ሚስት ለመኝታ ቸው ግልጽ ውይይት በማድረግ፤ በደስታ እንዲኖሩ መንገድ ለመጥ ረግ እሞክራለሁ። አንዳንዶቹ እሳቦች በአገራችን መጻሕፍት በብዛት ያልተጻፉ ይመስሉኛል። በተለይም በአማኞች ብዕር ብዙ አልተከተ ቡም። ምክንያቱም ከባሕሉ ተጽዕኖ የተነሳ አንደሆነ እገምታለሁ። ይሁን አንጅ ያህዌ የፈጠረው ቅዱስ ተግባር በመሆኑ፤ በድፍረት መገለጽ ይገባዋል።

ለመሆኑ <u>የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት /Sexual intercourse/ መቼ ነው የተፈጠረው</u> ? ከውድቀት በፊት ወይስ በኋላ? የሚሉትን ሁለት መሠረታዊ አሳቦችን በማንሳት አንቀጥል።

በዘፍጥረት መጽሐፍ ላይ በግልጽ አንደምንረዳው፤ እግዚአብ ሔር ሰውን የፈጠረው፤ ለራሱ ክብርና በረከት ነው። በእርግጥ ነው የፍጥረት ሁሉ እባትና አናት የሆኑት አዳምና ሔዋን፤ ተፈጥረው የተቀመጡትና ያረፉት በኤደን ገነት በሚያምር የአትክልት ስፍራ ነው። በታውም የዕረፍትና የሰላም፣ የደስታና የህሴት፣ ምንጭ መፍለቂያ በመሆኑ፤ ኤሎሂም/እግዚአብሔር የመጀመሪያው ሠርግ በኤደን አትክልት ስፍራ እንዲከናወን አደረገ።

ታዲያ ስለ ሩካቤ ሥጋ ግንኙነትና እጅግመር፤ ብዙዎች የተ ለያየ አሳብና ትምህርት የሚሰጡት፤ ከዚሁ አሳብ በመነሳት ነው። አብዛኛዎቹ የሩካቤ ሥጋ የተጀመረው ከውድቀት በኋላ ነው በማ ለት፤ ምክንያታቸውን በዘፍ. 4 ላይ በማነጣጠር «አዳምም ሚስቱን ሔዋንን አወቀ ጸነሰችም» ይላልና ሲሉ፤ ሌሎች ደግሞ አይደለም፤ የሩካቤ ሥጋ የተፈጠረው ከውድቀት በፊት በምዕራፍ 2 ላይ ነው። ምክንያቱም ከቁ. 23-25 ያለው ሕያው ቃል የሚያስረዳው፤ ስለ እውነተኛ ጋብቻና የሥጋ ግንኙነት ነው በማለት፤ መልሳቸውን በዚሁ አሳብ ያጸድቃሉ። ለማንኛውም ቃሉ የሚለውን እንመልከተ ውና፤ ለእያንዳንዱ መንፈስ ቅዱስ እንደ ገለጸለት የራሱን ውሳኔ ይስጥ።

> "አዳምም አለ «ይህቺ ኣጥንት ከኣጥንቴ ናት፣ ሥጋም ከሥጋዬ ናት፤ አርሷም ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባ ል። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። አዳምና ሚ ስቱ ሁለቱም እራቁታቸውን ነበሩ አይ ተፋፈሩም ነበር » ይላል። ዘፍ. 2:23-25

ለእኔ እንደሚገባኝ በዚህ ጥቅስ መሰረት፤ የሩካቤ ሥጋ የተፈጠረው ከውድቀትና ከኃጢአት በፊት መሆኑን ነው። እስካሁን በተረዳሁት መረዳት፤ የማምነውና የምደግፈው አሳብ ይህንን ነው። በቶሎ ለምን? ሳትሉ ተጨማሪውን መግለጫ እንመልከተው።

ይህንን አሳብ በመደገፍ በአዲስ ኪዳን እጉልቶ የሚናገረው ክፍል፤ በዕብራውያን 13:4 ላይ ያለው የጳውሎስ መገለጥ ነው። «መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹህ ይሁን» ይላል። ጳውሎስ በሁሉም ዘንድ ሲል፤ ከሰማይ በታች ባለ በምድር ፍጥረት ሁሉ፤ ማለቱ ነው። ጋብቻ ክቡር ከመሆኑም በላይ፤ ንጹህና ቅድስና ን የተሞላ ሕይወት ነው። ይህንን እውነት በሚገባ ከተረዳን፤ ስለ

ሩካቤ ሥጋ /Sex/ ያለን እመለካከት እንዲቀየር ያደርገዋል ብዬ እ ገምታለሁ። ከዚያም በአያንዳንዱ ችግር ላይ ለመወያየት እንድን ችል፤ የግልጽነትን ጉልበት ይጨምርልናል። በተጨማሪም በጠላት ላይ በመዝመት ትዳርን የሚያፈርሰውን ቁበኛ እውሬ፤ መትተን እ ንድንጥል ኃይልን ያጎናጽፈናል።

ዶ/ር ዶግላስ የተባሉት አሜሪካዊ የጋብቻ እውደ ጥናት ተመራማሪ ሊቅ ሲናገሩ ፡-

«በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ግብረ ሥጋ ግንኙነትና፤ እውነተኛ ጋብቻ፤ በፍጹም የሚለያዩ አይደሉም» በማለት፤ የሁለቱን ውህደትና አንድነት በአጠቃላይ ያስረዱናል። ግብረ ሥጋ ግንኙነት የራሱ ሕግና መመሪያ አለው። «የጋብቻ ሕይወት» በምትለው ትን ሽ መጽፍሐፌ ውስጥ፤ ሩካቤ ሥጋን በሚመለከት ትንሽ አሳቦችን እስፍሬያለሁ። ይሁንና በግብረ ሥጋ ግንኙነት ውስጥ፤ የወንድና የ ሴት ባህሪና አቀባበል ፈጽሞ የተለያየና የተራራቀ ነው።

ወንድ በፈለገው ጊዜ የፍትወት ስሜቱን በቀላሉ ሲያነሳሳ፤ ሴት ግን በተቃራኒው በፍጹም በችኮላ ልታደርገው አትችልም። ወ ንድ ሁልጊዜ የተዘጋጀ ሲሆን፤ ሴት ሁል ጊዜ ዝግጁ ልትሆን አት ችልም። ለምሳሌ በወር አበባ ጊዜ፤ ልጅ ወልዳ በምታጠባበት ጊዜ ፤ በእርግዝና ወቅት፤ በተለይም ወደ መጨረሻዋ ወራቶች አካባቢ ያሉት አስቸጋሪ ጊዜያቶቿ ናቸው። በሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ጊዜም፤ ራሷን ለባሏ አሳልፋ ለመስጠት ጊዜ ያስፈልጋታል።

<u>ችኩል ወንድ</u> ይህን ሳይረዳ በመቅረት፤ በግድ ይሁን በውድ፤ በፍቅርም ሆነ በጥላቻ፤ የራሱን ስሜት ያረካና፤ የእርሷን የፍትወት ስሜት ከምንም ሳይቆጥራሳት በመቅረት፤ ፊቱን ወደ ግድግዳ አዙ ሮ ይተኛል። ይልቁንም ያልረካችውን ሚስቱ እቅፍ መተኛትና እየ ደባበስ እንቅልፍ እንዲወስዳት ማድረግ ሲገባው፤ የራሱን አንቅልፍ ይለጥጣል። በልቡም ስለማትወደኝ ነው በማለት፤ መራራ ነገር

ማብቀል ይጀምራል። «ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል» እንዲሉ፣ ለጥፋቱ ሁሉ መነሻዋ እርሷ ናት በማለት ይደመድማል። በዚህ ሁኔታ እየቀጠለ ይሄድና፣ የትዳሩ መሠረት እየተናጋ፣ ቤቱ መንገድ ይጀምራል። የሚገርመው ግን፣ ብዙዎች ትዳራቸው መፍረሱን የሚያውቁት፣ የጋብቻው ወረቀት ሲቀደድ ነው እንጂ፣ የሩካቤ ሥጋቸው አለመጣጣም ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን አለመረዳታቸው ነው።

<u>የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለጋብቻ ሕይወት ነው</u>። እያንዳንዱ ተጋቢ፣ አንዱ ሌላውን ለማርካት መጣርና መጠንቀቅ ይገባዋል። ምክንያቱም በቤቱ ያልረካ ሰው፣ የሩካቤ ሥጋን እርካታ ለማግኘት ወደ ውጭ ሂዶ ሌላ ሰው በዓይኑ መቃኘቱ አይቀርምና ነው። ስለዚህ አማኞች ለግብረ ሥጋ ግንኙነት፣ ልዩ ጥንቃቄና ትኩረት እንዲሁም ጸሎት ያሰፈልጋቸዋል።

ከዚህ በታች በሩካቤ ሥጋ ያልረካ ሰው ባህርይ፣ ምን እንደ ሚመስል እንመልከት።

የግብረ ሥጋ አለመርካት ምልክቶች ከሆኑት ወስጥ ጥቂቶቹ፦

1. ያልረካ ሰው ሁልጊዜ ይነጫነጫል /ቁጠኛ/ ይሆናል
2. ወደ መኝታ ለመሄድ አይቸኩልም /አይናፍቅም/
3. የትዳር ጓደኛውን ይንቃል፣ ያጥላላል ያንቋሸሻል
4. ራሱን ይጥላል /ንጽህናውን አይጠብቅም/፣ ግድየለሽ ይሆናል
5. ከትዳር ጓደኛው ጋር አብሮ መብላት፣ መጸለይና መንገድ መሄድ አይፈልግም
6. በስማቸው አይጠራሩም/እርሱ፣ እርሷ፣ አንተ፣ አንቺ/ ይባባላሉ
7. በመኝታቸው ፊታቸውን እዙረው ይተኛሉ/አይተቃቀፉም/ ወይም አልጋ ይለያሉ

8. ለደቂቃ እንኳ ቁጭ ብለው መነጋገር አይችሉም
9. መዘጋጋት ይጀምራሉ /ሁሉ በዝምታ ያልቃል/ የማድ መልስ ካስፈለገም እንደ ዲዳ በጥቅሻ ይሆናል::
10. ስለ ትዳር ጓደኛቸው ደካማነትና መጥፎነት ለሌላ ሰው ያወራሉ

በሩካቤ ሥጋ የረኩት ደግሞ፣ የእነዚህን ተቃራኒ በማድረግ፣ የት ዳር ጓደኛቸውን ይንከባከባሉ:: ማለትም አብረው ይበላሉ፣ ይወያ ያሉ፣ ይተቃቀፋሉ፣ ይነፋፈቃሉ፣ መልካም ቃልን ብቻ ስለ ትዳር ጓደኛቸው ይናገራሉ፣ ይተሳሰባሉ፣ ስጦታ ይለዋወጣሉ፣ አብረው ይ ጸልያሉ፣ ይረዳዳሉ ወዘተ ...::

ዶ/ር ዊለርድ ሃርሊ የተባሉት አሜሪካዊ ሊቅ፣ ስለ ቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶች ባጠኑት ጥናት ሲናገሩ፣ ለባልና ለሚስት መጣ መር አምስት ዋና ዋና ነጥቦችና ምክንያቶች የሚባሉት፣ የሚከ ተሉት ናቸው ይላሉ::

ለሚስት አምነቱ ዋና ፍላጎቶቿ	ለባል አምነቱ ዋና ፍላጎቶቹ
1. ፍቅር	1. የግብረ ሥጋ ግንኙነት
2. ግንኙነትን፣ውይይትን፣ቋንቋ ለቋንቋ መግባባትን	2. የምታዝናና ጓደኛ
3. ግልጽነትን ወይም ታማኝነትን	3. የምትስብ ሚስት
4. የገንዘብ ድጋፍን	4. ዋና ዋና በሆኑ ጉዳዮች ላይ የምታግዝ
5. ለቤተሰቡ የተሰጠ ባልን	5. ለሚያደርገው ሁሉ አድናቆትን የምትሰጥ

ከዚህ በላይ የተገለጹት አስር የሴትና የወንድ ፍላጎቶች፣ ከ ተሟሉ በትዳር ውስጥ ብዙ ችግር እንደማይፈጠር ያረጋግጣሉ።

6-2. የግብረ ሥጋ ግንኙነት በረከት ነው!

> «ከጉድጓድ ውኃ፣ ከምንጭህም የሚፈልቀውን ውኃ ጠጣ። ምንጮችህ ወደ ሜዳ ወንዞችህ ወደ አደባባይ ይፈሳሉን? ለአንተ ብቻ ይሁኑ ከአንተ ጋር ሳሉ እንግዶችም አይሁኑ። ምንጭህ ብሩክ ይሁን፣ ከጉብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበል ህ። እንደ ተወደደች ዋላ እንደ ተዋበችም ሚዳቋ ጡትዋ ሁልጊዜ ታርካህ፣ በፍቅሯም ሁልጊዜ ጥገብ።»
>
> ምሳሌ 5:15-19

ውኃ ሕይወት ነው። ጥምን ከማርካቱና ፍጥረትን ሁሉ እንዲንቀሳቀስ ከማድረጉም ባሻገር፣ ቆሻሻን ያስወግዳል፣ ይፈውሳል፣ ያረስርሳል። ፍሬ እንዲገኝ ያደርጋል። ጥበበኛው የግብረ ሥጋን ግንኙነት ያለ ነገር በውኃ አልመሰለውምና፣ በጥቅሱ ላይ ዓይንን ጣል አድርጉ፣ እያንዳንዱን ቃል መመርመር ተገቢ ነው።

በተጨማሪም ውኃ አዲስን ሕይወት ይሰጣል። ድካምንና ጭን ቀትንም ያስወግዳል። መንፈስ ቅዱስም በውኃ ይመሰላል። በስጦታ ው ያረካልና። ጸሐፊው እንደሚለን፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደ ውኃ ጉድጓድ ነው። በየጊዜው የሚጠጣና የሚረኩበት። የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሰውን ማንነት ይቀይራል። አመለካከትንና አሳብን ያሻሽላል። የሩካቤ ሥጋ የሚያልቅና የሚጨርስ አይደለም። ጌታ ሲፈጥረው የረጅም ጊዜ ዕድሜ እንዲኖረው አድርጉ ነው። ሰውም ተጠንቅቆ መያዝ ያለበት ለዚህ ነው።

እውነቱን እንነጋገርና፣ ለወንድ ከሩካቤ ሥጋ የበለጠ ታላቅ መፈተኛ አለ፣ ሰማለት እያስደፍርም። ምንም እንኳን ሴቶችም በዚሁ ጉዳይ ቢፈተኑም፣ በወንዱ ፈተናው እንደ ሚያይል የጋብቻ

ተመራማሪዎቹ ይጠቁማሉ። እርግጥ ነው በየቀኑ ባውሳላው መንገድ ላይ፣ ላይና ታች የሚለው የአዳም ዘር ሁሉ፣ ከሚያየውና ከሚያሸተው የሽቶ ጠረን፣ ሳይፈተን እንደማይውል የታወቀ ነው። ምንም እንኳ በልቡ የሚመላለሰውን ሁሉ ያደርገዋል ወይም ይናገረዋል ባንልም፣ የፍትወት ስሜቱን እንደሚቀሰቅስበት ግን ሳይታለም የተፈታ ነው። ለዚህ ነው መነኩሴዎች ከገዳም እንዳይወጡ የሚገደዱት። ጌታም ይህን አሳብ በወንጌል ላይ በግልጽ አስተምሯል።

> « ---እኔ ግን እላችኋለሁ፣ <u>ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም</u> ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሮአል » ማቴ-5:28 በማለት፣ ከብሉይ ኪዳን ሕግ በማስበለጥ አጠንክሮታል።

ማየት የሁሉም ችግር ስለሆነ፣ መፍትሄው፡- ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው፣ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ምኞቱ ጋር መስቀልና፣ ከጌታ ጋር መስማማት ነው። ሌላው ደግሞ፡- ባልና ሚስት የፍትወት ስሜታቸው በተነሳባቸው በማንኛውም ጊዜ፣ የሩካቤ ሥጋ መፈጸም ይገባቸዋል። ጳውሎስ ይህን ችግር ስለተረዳ ነው «<u>አትከሳ ከሱ</u> »ያለው።

ባልና ሚስት በእማካኝ <u>በሳምንት ሁለት</u> ጊዜ፣ የሩካቤ ሥጋ መፈጸም ይገባቸዋል። እንደዚህ የሚያደርጉ ከሆነ ከምንዝርናና ከዝሙት ጠንቅ ይድናሉ። በእርግጥ ይህን ህግ እናድርገው ባልልም፣ መልካም ተግባር ነው እላለሁ። በሩካቤ ሥጋ ውስጥ ደስታንና እርካታን በመለማመድ፣ እግዚአብሔርን ማመስገን ይገባል። ምክንያቱም ምንጩ እርሱ ነውና።

ፍቅር ለግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደ ዘይት በመሆን፣ በቀላሉ ያለ ምንም ችግር በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ኃይል አለው። ፍቅር እየጨመረ በሔደ ቁጥር፣ የሩካቤ ሥጋ ፍላጐትም፣ በእጥፍ እያደገ ይሔዳል። ከሚስትህ ጋር የምታደርገውን የሩካቤ ሥጋ ጌታ ያከብረዋል። በፈለከው ጊዜ ብትጠቀም ኃጢአት የለብህም። በቀ

ንም ይሁን በማታ ነጻነት ተሰጥቶኃል። አንዳንዶቹ እንደሚያስቡት የጨለማ ስራ አይደለም። እኛ የብርሃን ልጆች ስለሆን፤ በብርሃን መመላለስ አለብን።

ከመጽሐፈ ምሳሌ ፀሐፊ የምንረዳቸው፤ አምስት ዋና ዋና አሳቦች የሚከተሉት ናቸው።

1- ከምንጭህ /ከሚስት/ ሁልጊዜ ጠጣ /ዕርካ/። ሌላ ሴትና ኃለሞታ አትመልከት። ምክንያቱም ከኃለሞታ ሴት፤ ምንም ከሚስትህ የተለየና የተሻለ ነገር አታገኝም። ይልቁንም ኃጢያትንና በሽታን ታተርፋለህ እንጅ። የኤልዛቤል አይነት የግልሙትና ቅባትና ሽቶ፤ በጌታ መንፈስ የተመረጠንና የተቀባን ጀግና፤ ሊበግር አይገባውም። ከእዩ ሕይወት የምንማረው ይህንኑ አይነት ቆራጥነት ነው። 2ነገ 9:30-37

2- ለአንተ ብቻ ሚስትህ ትሁን፤ ያንተው የግልህ ናትና እርካባት። ሚስትህን አትቀይራትም፤ አታውሳትም። ወይም በስጦታ ለወዳጅ አታስተላልፋትም። በምድር ላይ ለግልህ ብቻ አንድትሆን የተሰጠችህ ብቸኛ ንብረትህ ናት። «<u>በሚስትና ባገር ቀልድ የለምና</u>» የሚለው ያባቶቻችንን ቀረርቶ፤ እውነትነት እንደለበት አትዘንጋ።

3- ከጉብዝናህ ሚስት ጋር <u>ደስ ይበልህ</u>፤ ደስታን የምትገድለውና የምታድነው አንተው ራስህ ነህ። ስለዚህ ከሚስትህ ጋር <u>ደስታን ተለማመድ</u>። ንግግርህና ድርጊትህ ወደ ደስታ የሚያመራ ይሁን። ደስታ የነፍስንና የመንፈስን አስራት ይበጥሳል። የሩካቤ ሥጋ ባዘነ ሰው ሕይወት ውስጥ ጊዜያዊ ደስታን ያፈልቃል። አንድ ጊዜ አዲስ አበባ እያለሁ፤ ጫማዬን በማስጠርግበት ጊዜ፤ አንድ ወጣት ያለውን በፍጹም አልረሳውም። ያለውም እንዲህ ነው። «<u>ከሴት ጋር የሩካቤ ሥጋ ስፈጽም፤ ዓለምን የተቆጣጠርኩ ይመስለኛል</u>» አለ። በእርግጥ መሰለው እንጅ፤ ዓለ

ምን አልተቆጣጠረም። ይሁንና የተስማውን ደስታ በራሱ ቋንቋ ማሰረዳቱ ነው። አንተም ሁልጊዜ ደስ እንዲልህ ሚስትህን አስ ደስታት።

4- ጡጅ <u>ሁልጊዜ ያርካህ</u>፤ የማያቋርጥ የሩካቤ ሥጋ እርካታ ተፈቅ ዶልሃል። እእምሮህንና ልብህን ወደ ጡቶቿ በማዝለቅ፣ እውነ ተኛ እርካታንና ደስታን፣ ዕረፍትን፣ ከሚስትህ አካል ውስድ፣ ማለቱ ነው። ስለዚህ እወቅበት።

5- በፍቅሯ <u>ሁልጊዜ</u> ጥገብ፤ እየደጋገመ ሁልጊዜ የሚለው በሚገባ ትኩረት እንዲሰጠው ነው። አስፈላጊነቱንም ለማጠንከር ስለሆነ፤ አዘውትረህ አፍቅራት። ፍቅር ሞቅ ያለ አድናቆትንና ስሜትን ስለሚቀሰቅስ፤ ፍቅርን አበክረህ ተለማመድ።

የአዲስ ኪዳኑ ሐዋርያ ወንድማችን ጳውሎስ፤ የሚለውን ደግሞ እንስማ። 1ኛ ቆሮ. 7:2-5

> «ነገር ግን ስለዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ <u>ለራሱ ሚስት</u> ትኑረው፣ ለእያንዳንዲቱ ደግሞ <u>ለራሷ ባል</u> ይኑራት፤ <u>ባል</u> ለሚስቱ <u>የሚገባትን</u> ያድርግላት፣ እንዲሁም ደግሞ <u>ሚስቲቱ</u> ለባልዋ። <u>ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም</u> ሥልጣን ለባሏ ነው እንጂ። እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ስልጣን የለውም። ስልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ፣ <u>ለጸሎት ትተጉ ዘንድ</u> ተስማምታችሁ ካልሆነ በቀር፣ እርስ <u>በዕርሳችሁ አትከላከሉ</u>። ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተ ናችሁ ደግሞ፣ አብራችሁ ሁኑ።»

- ከትዳር ጓደኛ ጋር የሚደረግ የሩካቤ ሥጋ፤ ከመመኘትም ሆነ ዝሙት ከማድረግ ይከለክልሀል።

- የባልና የሚስት ጉዳይ፤ የግል ሕግ ነው እንጂ፤ የጋራ አይደ ለም። ሚስት ለአንድ ለባሏ ብቻ ናት። ባልም ለሚስቱ ብቻ።

- ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት። በሥጋም በነፍስም ይንከባከባት። ሚስትም እንደዚሁ ባሏን ትንከባከበው።

- ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም። ሙሉ በሙሉ ለባሏ ራሷን አሳልፋ መስጠት አለባት። ባልም እንደዚሁ፦ ለሚስቱ ራሱን አሳልፎ ይስጥ። ማለትም ባል የሚስቱን አካል እንደ ራሱ አድርጎ በመቁጠር በፈለገው ጊዜ ይጠቀምበት ሲሆን፤ ሚስትም ደግሞ በባሏ ገላ ላይ በመሰልጠን፤ ስሜቷ በተነሳባት ጊዜ ፍላጎ ቷን ለማርካት ትጠቀምበት ማለት ነው።

  እርግጥ ነው፤ የአገራችን ሴቶች ይህን ያህል መብትና ነጻነት እ ንደማይሰማቸው የታወቀ ነው። የሰለጠኑት አገር ሴቶች ግን፤ በሚገባ በዚህ መመሪያ ስለሚጠቀሙበት፤ ምንም እይነት የሩካ ቤ ሥጋን ፍላጎት ከማንጸባረቅ የሚከለክላቸው ይሉኝታ የለባቸ ውም። ስለዚህ እህቶቻችን የውስጥ ስሜታችሁን አፍናችሁ ይዛ ችሁ ከምትጨነቁ፤ ለባላችሁ አሳባችሁን በመግለጽ፤ የወሲብ ድ ርሻችሁን ተወጡ።

- ለጸሎት ተስማምታችሁ ካልሆነ በቀር፤ ለሩካቤ ሥጋ መከላከል አይቻልም። በዚህ አጋጣሚ ከባል /ከሚስት/ ፈቃድ ውጪ፤ <u>የሦስት ቀንና የሳምንት ወይም የበዛ ጾም ጸሎት ማድረግ ትክ ክል አይደለም</u>። ጌታም አይከብርበትም። በመጀመሪያ ከባልሽ /ከሚስትህ/ ጋር መመካከርና መተማመን ያስፈልጋል። እንተ ታስረሀል። በራስህ ምንም ልታደርግ አትችልም። ጸሎቱና ጾሙ መልካም ሆኖ ሳለ፤ በመስማማት አለመደረጉ ግን፤ መስዋዕቱን ከጣራ በላይ አልፎ እንዳያርግ ያደርገዋል።

  በተለይ ከአንዳንድ ተጋቢዎች ዘንድ እንደሰማሁት፤ ከማይጣጣም የሩካቤ ሥጋ ለማምለጥ፤ ጾም ጸሎትን እንደ መከላከያ መሳሪያ አድርገው እንደሚጠቀሙ ለማወቅ ችያለሁ። ይህ ተቀባይነት የ ሌለው ኃጢያት ነው። በዚህ እይነት ውስጥ ያላችሁ ስዎች ብ

ትኖሩ፤ ወደ ጋብቻ አማካሪዎች ሄዳችሁ መፍትሄ ብትፈልጉ መልካም ነው እላለሁ።

- ባልና ሚስት አብረው ሊቀመጡና ዘመናቸውን ሊጨርሱ ስለሆነ የተጋቡት፤ አስገዳጅ ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ ባልና ሚስት ተለያይተው መኖር የለባቸውም፡ በገንዘብና በሥራ ዝው ውር ምክንያት መለያየቱ፤ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። ለቤተሰቡ የተሻለ ሕይወት ለማምጣት ሲል፤ ከአምስት ዓመት በላይ በውጭ አገር በበረንዳ እያደረ፤ የሚያገኘውን ገንዘብ ሁሉ ለሚስቱና ለልጁ ሲልክ ከርሞ፤ በመጨረሻ ዘወር በል ተብሎ የተባረረ ወንድም አውቃለሁና ነው። ገንዘብ ለማግኜት ብላችሁ አላስፈላጊ ያልሆነ መስዋዕትነት ባትከፍሉ፤ መልካም ነው። ገንዘብ ባልን ወይም ሚስትን አይተካም።

የሩካቤ ሥጋን ብልጽግናና ጌጣጌጥ፣ ልብስ በፍጹም አይተካውም። በቁሳቁስ ነገር በመመርኮዝ ትዳራችሁን እትጉዱ። ይልቁንም የተለ ያዩ የጋብቻ ነክ ጽሁፎችንና ሴሚናሮችን በጋራ በመሳተፍ፡ የሩካቤ ሥጋ አጠቃቀምን ትምህርት መውሰዱ፤ ፍቅራችሁንና ቤታችሁን ያጸናላችኋል።

ባጠቃላይ «አትከሳከሉ» የሚለውን በዚህ ሁኔታ ለማየት የሞከር ነው፤ በጣም አስፈላጊ ከፍል በመሆኑ ነው። የግብረ ሥጋ ግንኙነት፤ ለጋብቻ ዋና ማጣፈጫ ቅመምና፣ ሕይወት ነው። ስለዚህ በሚገባ ሊከናወንና ለደስቱበት ይገባል። በዘፈቀደ የሚታይና የሚተው ጉዳ ይ አይደለም። ባልና ሚስት ለወሲብ ፍላጎታቸው ግልጽና አውነ ተኞች መሆን ይገባቸዋል። የባልና ሚስት መኝታ መባረክ፤ የትዳ ሩ መባረክ ዋና መለኪያ ነው። ስለዚህ ከዚህ በታች ያሉትን እንደ ገና አተኩሩባቸው።

ለሩካቤ ሥጋ አለመጣጣም ዋና ችግሮች

1. የግብረ ሥጋን ግንኙነት እንደ ኃጢያት መቁጠር

2. አንዱ የሌላዋን ስሜትና ፍላጐት አለመጠበቅና አለማርካት
3. ለግብረ ሥጋ ግንኙነት ቅድመ ዝግጅት አለማድረግ
4. ፍቅር የሌለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም
5. ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት አለመወያየትና፣ መፍትሔ ከአማካሪዎች አለመጠየቅ:: የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ለሩካቤ ሥጋ መጣጣም መፍትሄዎቹ ደግሞ:-

1ኛ ቆሮ. 7:1-7 መመሪያዎች

1. የተጋባችሁት ስለዝሙት ጠንቅ መሆኑን መረዳት
2. ባል ለሚስቱ የሚገባትን ማድረግ
3. በራስ ሥጋ ላይ ባልም ሆነ ሚስት ሥልጣን እንደሌላቸው ማወቅ
4. ለያምና ለፀሎት ካልሆነ በስተቀር፣ ሁልጊዜ መፈቀዱን ማወቅ:: ጸም ጸሎቱም ሁለታችሁ ተስማምታችሁ ካልሆነ፣ መከናወን እንደሌለበት መረዳት::
5. የተለየ ችግር በአካል ላይ ከሌለ በስተቀር፣ መከላከል እንደማትችሉ መገንዘብ::
6. አብራችሁ ሁኑ:-ለገንዘብ ብላችሁ አትለያዩ

ምሳሌ 5:15-19

1. ምንጭህ ብሩክ ይሁን
2. ከሚስትህ ጋር ደስ ይበልህ
3. እንደ ተወደደች ዋላ እንደ ተወደደች ሚዳቋ ትሁንልህ
4. ጡቷ ሁልጊዜ ታርካህ:: አሜን::
5. በፍቅሯ ሁልጊዜ ጥገብ

መዝ. 128:1-6 ሚስትህ በቤትህ ውስጥ እንደሚያፈራ ወይን ናት:: ተፈወስባት::

ወይንን :- ትጠጣዋለህ፤ ትበላዋለህ፤ ትፈወስበታለህ፤ ኃዘንን ታርቅ በታለህ፤ በጥላው ታርፋለህ፤ ደስታህን ትገልጽበታለህ። ሚስ ትም እንደ ወይን ትሁንልህ።

መክ. 9:7-9 በምድር ዕድል ፈንታህ ከሚስትህ ጋር መደሰት ነው። ስለዚህ እቅምህ እንደ ፈቀደልህ፤ እንደ ሚስትህ ችሎታና ኃይልህ፤ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ዕርካ።

አስታውሱ! በባልና ሚስት መካከል የሚደረግ የሩካቤ ሥጋ፤ ንጹህና ቅዱስ፤ በእግዚአብሔርም የተወደደ ነው። ዕብ. 13:4 መኝ ታውም ንፁህ ይሁን። ትዕዛዝ ነው!



ግብረ ሥጋን የሚፈታተኑ ችግሮች

የግብረ ሥጋን የሚፈታተኑ ብዙ ችግሮች አሉ። ይሁንና የጎሉትንና የሕብረተሰባችን መሰናክል የሆኑትን፤ በአራት ክፍሎች በመክፈል፤ ከዚህ በመቀጠል እናያቸዋለን። እነርሱም፡- *መንፈሳዊ፣ ባሕላዊ፣ የባሕርይና የጤና ችግር* የሚሉት ናቸው።

፯-1 መንፈሳዊ ችግሮች፡-

ሀ- እንደ ኃጢአት መቁጠር

በተለይም ብዙ ጸሎት የሚያበዙና መንፈሳዊነት የሚሰማቸው ሰዎች፤ ከጸሎት በኋላ ወደ ሩካቤ ሥጋ መሄድ፤ መርከስ ነው ብለው ስለሚያስቡ ራሳቸውን ለመስጠት ይቸገራሉ። ይልቁንም ሴቶች ። ወንዶችም ቢሆኑ የዚህ አይነት ችግር ይጠናወታቸዋል። ለምሳሌ አንዳንድ አገልጋዮችና ሰባኪዎች፤ ከሚስት ጋር የሩካቤ ሥጋ ፈጽሞ መስበክ፤ ቅድሰናን ያረክሳል ብለው ስለሚያስቡ፤ ለሦስት ቀን ወይም ለሳምንት፤ ከሚስታቸው ራሳቸውን በመለየት፤ የሚስቶቻቸውን ስሜት ይጎዳሉ።

እነዚህ አገልጋዮች ያልተረዱት ነገር ቢኖር፤ እነ ኬፋ <u>ሚስቶቻቸውን ይዘው እንደ ዞሩ መርሳታቸው ነው</u>። ሌሎች ደግሞ በብሉይ ኪዳን ስርአት ያሉ ስለሚመስላቸው፤ ዳዊት ለካህኑ ለአብ ያትር ሦስት ቀን ከሴቶች ተቀድሰናል፤ እንዳለው ለማለት ይመስላል፤ ሦስት ቀን ወደ ግድግዳ በመዞር ይተኛሉ። 1ሳሙ-21:5 ይህ አይነቱን ድርጊት በትዳር ጓደኛ ላይ እንዲከናወን፤ መጽሐፍ ቅዱስ

አይፈቅድም። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ያለውን ማርከስ ትልቅ ኃጢያት ስለሆነ፤ መጠንቀቁ መልካም ነው እላለሁ።

ለ- ራስን ወዳድ መሆን

የሩካቤ ሥጋ የጋራ እንጂ የግል ብቻ አይደለም። ያ ቢሆን ኖሮ ሰው ብቻውን መርካት በቻለ ነበር። አዳም ብቻውን በነበረ ጊዜ ፈቱ አልፈካም። ተመቸኝ ብሎ አልተቀመጠም። ለዚህ ነው ኤሎሂም/እግዚአብሔር «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም» በማለት ሔዋንን ያመጣለት።

ወንዶች በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ትምህርት ያስፈልገናል። ራስ ወዳድነት ብዙውን ጊዜ የሚያጠቃው እኛኑ ነውና። ወንድ ለመርካት ብዙ ጊዜ አያስፈልገውም። ከረካ በኋላ ደግሞ ሚስቱን የ ማርካት ኃይል አይኖረውም። ስለዚህ ስሜቱን በመቆጣጠር፤ ለባለቤቱ የሚጠቅመውን መፈለግ ይገባዋል። 1ኛ ዮሐ. 4:16 «እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባ ናል» ይላል። እውነተኛ ፍቅር ይህን ያደርጋል እንጂ፤ «እኔ <u>ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል</u>» አይልም።

ከዚህም በተጨማሪ ለወንዶች የምሰጠው ምክር፤ ሴቶች ከሩካ ቤ ሥጋ በፊት መተሻሸትን መደባበስን እንደሚወዱ ማወቅን ነው። መውደድ ብቻ ሳይሆን ተፈጥሯቸው ያስገድዳቸዋል። ስለዚህ ስሜ ታዊ የሆኑ ቦታዎችን፤ ማለትም እንደ፡- ጭናቸውን፣ ጡታቸውን፣ ቅንድ ባቸውንና አፍንጫቸው አካባቢ ለስላሳ በሆነ ዳስሳ፣ መዳሰሱና መሳሙ፣ ፈቃዳቸውን ሙሉ በሙሉ፣ ለባላቸው አሳልፈው እንዲሰ ጡ ያደርጋቸዋል።

«በአፉ መሳም ይሳመኝ፤ ፍቅርህ ከወይን ጠጅ ይልቅ መልካ ም ነውና» መኃ. 1:2 የሚለው ሕያው ቃል፤ የሴቶች የልብ

ፈቺኽት መሆኑ መዘንጋት የለበትም። እንግዲህ ቃሉ እንደዚህ ካዘዘ፣ በተግባር ተርጉሞ መደሰቱ የሰው ትልቁ ተግባር ነው።

ሐ. መፈራራት

> «ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጅ በፍቅር ፍር ሃት የለም፣ ፍርሃት ቅጣት አለውና፣ የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም።» 1ዮሐ 4፣18

በኢትዮጵያውን ባሕል መሠረት፣ ባልን እርስዎ እያሉ መጥራት የተለመደ ነው። አክብሮቱ መልካም ሆኖ ሳለ፣ የመቀ ራረብንና የአንድ አካል ክፍልነትን በግድግዳ እንዲከፈል ያደር ጋል። ባልና ሚስት እንደ ጓደኛም እንደ ቤተሰብም መጫወትና መቀላለድ አለባቸው።

ሚስት የሚሰማትን፣ ለባሏ በቀልድና በፈገግታ መግለጽ መቻ ል አለባት። ባልም ሚስትን እንደ ዕቃ /ግዑዝ/ ነገር ሳይመለከት፣ ማጫወት ይጠበቅበታል። የሰለጠነው ዓለም ለሴቶች ያላቸው ቦታም በጣም በዝቷል። በኢትዮጵያ ደግሞ ለሴቶች የተሰጣቸው የበታች ነት ስሜት አለቅጥ በዝቷል። ከሁለቱም ሰው ሰራሽ ሕግ በመው ጣት፣ እንደ አምላካችን ድንጋጌ መራመዱ ችግሩን በቀላሉ ይፈታ ል ብየ አምናለሁ።

በአገራችን የብዙ ባልና ሚስቶች ችግር *ፍርሃት* ነው። የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚሰምረው፣ በእውነተኛ ነጻነት ሲከናወን ብቻ ነው። ይሁን እንጅ ብዙ ባልና ሚስቶች ስሜታቸውን ለመግለፅ ስለሚ ፈራሩና ስለሚሸማቀቁ፣ ብዙ ችግር ይደርስባቸዋል። ለፍርሀታቸው መነሻ ከሆኑት ምክንያቶች ውስጥ ጥቂቶቹ፡-

- ይሉንታ ስለሚያጠቃቸው
- ሃፍረት ነው ብለው ስለሚያስቡ

- አልሰማም ወይም አሳቤን አይቀበለውም ብለው ስለሚያስቡ
- ቢቆጣስ ስለዚህ ባልናገረው ይሻላል (ከነገሩ ጦም ማደሩ) በማለት
- ችግሬን አይረዳውም
- ይንቀኛልና ብተወው ይሻላል ወዘተ--የመሳሰሉት ናቸው ::

ይሁን እንጅ እነዚህ ሁሉ፤ ከፍቅር በታች እንጅ በላይ ስላል ሆኑ፤ ጊዜና ሁኔታን እየጠበቁ በድፍረት መነገሩ መፍትሄ ያስገኛ ል:: በልብ ይዞ ለብቻን ማብሰልሰሉ ግን፤ በሽታ ከመፍጠር በስተቀ ር የሚያመጣው ጥቅም የለም:: አስታውሱ ፍርሃት ቅጣት አለበት ነው የሚለው ቃሉ:: ስለዚህ ከትዳር ጓደኛችሁ ጋር በድፍረት በመ ነጋገር ከቅጣት ዳኑ::

እውነተኛ የሩካቤ ሥጋ ፈውስ፤ በቃል ከሚወረወር ቀልድና ሙገሳ ይመነጫል:: በዚህ አጋጣሚ ለባል አንድ ምክር ብለግስ ደስ ይለኛል:: ክዚህ በታች ያለውን ጥቅስ፤ ድምጽህን ከፍ አድርገህ፤ ዓይን ዓይኗን እየተመለከትክ ለሚስትህ አንብብላት::

> «ወዳጄ ሆይ እነሆ ውብ ነሽ፤ እነሆ አንቺ ውብ ነሽ፤ በዓይነ ርግብ መሸፈኛሽ ውስጥ ዓይኖችሽ እንደ ርግቦች ናቸው፤ ጠጉርሽ በገለአድ ተራራ እንደሚወርድ አንደ ፍየል መንጋ ነው:: ጥርሶችሽ ታጥበው እንደ ተሸለቱ ሁሉም መንታ እንደ ወለዱ ነውርም የለብሽም::» መኃ. 4:1-7

በማለት እየደባበስክ አስደስታት:: ይህን ማድረግ ስትጀምር፤ የባለቤትህ ሁኔታ በብዙ ይቀየራል:: በል እንግዲህ ወንድሜ ጌታ ይርዳህ!

መ- ሦስተኛ ሰው ጣልቃ ማስገባት (ዝሙት)

ይህ በብዛት የሚታየው በማያምኑ ሰዎች ላይ ቢሆንም፤ ለት ምህርታችን ይሆን ዘንድ አብሬ ልጠቅሰው ወደደኩ:: በብሉይ

ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን፣ እምላካችን አጥብቆ ከሚጸየፈው ኃጢያት ውስጥ አንዱና ዋነኛው፣ ከባል ወይም ከሚስት በላይ ወደ ሌላ ሰው ሂዶ የሚፈጸምን የሩካቤ ሥጋን ነው። በብሉይ ኪዳን ወዲያውኑ ሲያስወግር፣ በአዲስ ኪዳን ደግሞ፣ ምሕረት የማይሰጠው ወደ ሲኦል የሚያስከትት ከፍተኛ ወንጀል ነው። አንዳንዶቹ የሚመስላቸው ከተለያዩ ሴቶች ወይም ወንዶች ጋር ቢተኙ፣ የሩካቤ ሥጋ ስሜታቸው የማረካ ይመስላቸዋል። እንዲያውም አንዳንዶቹ ለምን ይህን ታደርጋላችሁ? ተብለው ሲጠየቁ፣ የሚሰጡት ምላሽ ቢኖር፣ ሁልጊዜ ሽሮ ወይም ሥጋ መብላት እንደሚሰለች ሁሉ፣ አንድ ሴት ወይም ወንድ ይሰለቻል ይላሉ።

የጌታ ቃል በምሳ 30፣12 «ለራሱ ንጹሕ የሆነ፣ ከእርኩሰቱ ያልጠራ ትውልድ አለ » ስለሚል፣ መቼስ ለእነዚህ ሰዎች ከመጸለይ በስተቀር፣ በሰይጣን መንፈስ ስለተለከፉ በምክር መመለስ አይቻል ም። ምናልባት እነዚህ ሰዎች የሰሎሞንን አስከፊ ውድቀት ቢማሩ ይሻላቸዋል እላለሁ። ምክንያቱም ሰሎሞን ወደ ሺህ የሚጠጉ ሴቶች ን አግብቶ እርካታ ሳያገኝ ቀርቶ፣ ሁሉም ከንቱ ነው በማለት ሞቷ ልና ነው። የሆነው ሆኖ የጌታ ቃል እንደሚነግረን፣ ከትዳር ጓደኛ ውጭ የሚደረግ ወሲብ፣ ትልቅ ኃጢያት ነውና መመለሱና ንስሐ መግባቱ ከፍርድ ያድናል።

> «ማንኛውም ሰው ከሌላ ሰው ሚስት ወይም ከባልንጀራው ሚስት ጋር ቢያመነዝር፣ አመንዝራውና አመንዝራይቱ ፈጽመው ይገደሉ » ዘሌ. 20:10

> «ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድ ባቸዋል።» ዕብ-13:4

> «ወደ ሰው ሚስት የሚገባም እንዲሁ ነው፣ የሚነካትም ሁሉ ሳይቀጣ አይቀርም። ... ከሴት ጋር የሚያመነዝር ግን አእም ሮው የጎደለ ነው፣ እንዲሁም የሚያደርግ ነፍሱን ያጠፋል።» ምሳሌ 6፣27-32

7-2 ባሕላዊ ችግሮች

ሀ- የሴቶች ግርዘት

የእያንዳንዱ አገር የራሱ የሆኑ ጠቃሚና ጎጅ ባሕሎች አሉት:: በእኛም አገር ሁለቱም አይነት ባሕሎች አሉን:: ጎጅ ከሚ ባሉት ውስጥ አንዱ የሴቶች ግርዘት ነው::

በዘፍጥረት 17 ላይ እንደምንረዳው፤ ያህዌ/እግዚአብሔር ግርዘትን የሰጠው፤ ለወንዶች ብቻ ነው:: ያም ደግሞ የዘለአለም ቃል ኪዳን ምልክት በመሆን፤ እግዚአብሔርንና አብርሃምን ለማ ቆራኘት የተገባ መኃላ ነው::

> «ከእናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ፤ የቁልፈታቸውንም ሥጋ ትገ ርዛላችሁ፡ በእኔና በእናንተ መካከል ላለውም <u>ቃል ኪዳን ምልክት</u> ይሆናል:: » ዘፍ-17:10-11

የቁልፈታቸውን የሚለውን ማሰቡ መልካም ነው:: ወንዶች በተፈጥሯቸው ላይ የተቆለፈ ነገር ስላለ፤ መቆረጥ አለበት:: በሴቶች ግን ምንም ቆላፋና መቆረጥ የሚገባው አካል የለም:: የቃሉን አላ ብ ስንቀጥል፤ ግዝረቱ በወንዶች ላይ መቼ መከናወን እንዳለበት ሲ ያስረዳ እንዲህ ይላል::

> «የስምንት ቀን ልጅ <u>ይገረዝ፤</u> በቤት የተወለደ ወይም ከዘራችሁ ያየደለ፤ በብርም ከእንግዳ ሰው የተገዛ <u>ወንድ ሁሉ፤</u> በትውልዳቸው ይገረዝ:: በቤትህ የተወለደ በብርም የተገዛ ፈጽሞ ይገረዝ:: ቃል ኪዳኔም <u>በሥጋችሁ</u> የዘላለም ቃል ኪዳን ይሆናል» ዘፍ. 17:12-13

ከዚህ ሕያው ቃል ውስጥ እንደምንረዳው፤ <u>ግርዘት</u>:-

1- የቃል ኪዳን ምልክት ነው፡ ምክንያቱም ደም ይፈሳልና ነው።

2- የሥጋ ማህተም ነው። የመሃላ ልጅ መሆኑን ያሳያል።

3- የነጻነት ምልክት ነው። ምክንያቱም የማይጠቅመው ክፍል ተቆርጦ ወድቋልና

4- የትዕዛዝ ፍጻሜ ነው። እግዚአብሔር ያዘዘው የግድ መፈጸም ያለበት ተግባር ነውና። ወንድ ሆኖ ባይገረዝ የሚደርስበትን ቅጣት ደግሞ ሲያስረዳ፤ እንዲህ ይላል። «የቁልፈቱን ሥጋ ያል ተገረዘ ቆላፍ ሰው ሁሉ፤ ያቺ ነፍስ ከወገኗ ተለይታ ትጥፋ። ቃል ኪዳኔን አፍርሳለችና። » ዘፍ 17፣14

ልብ በሉ! እግዚአብሔር ለተናገረው ነገር ቆራጥና ጨካኝ ነው። በቃል ኪዳን ውስጥ መኖር ላልፈለገ ሁሉ፤ ያዘዘለት ሞትን ነው። ምክንያቱም፡- ሰውየው ራሱ ከቃል ኪዳን ውጭ ለመሆን መርጧልና ነው። <u>ግን ወንድ ሁሉ አለ እንጅ፤ ሴት ሁሉ አላለም።</u> እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ግርዘት የሚያስተምረን እንዲህ ከሆነ፤ ለምንድን ነው በአፍሪካ ወይም በአገራችን ሴቶች የሚገረዙ ት? ምንም እንኳ እንዴት አንደ ተጀመረና ማን እንደ ጠነሰሰው ግልጽ የጽሑፍ መረጃ ባይኖረንም፤ ከአፈ ታሪክ እንደምንረዳው፤ የሴቶች የፍትወት ስሜት ከፍተኛ በመሆኑ፤ አመንዝራዎችና ባለጌ ዎች እንዳይሆኑ ለመከላከል ነው ይላሉ።

እነዚህ ሰዎች ያልተረዱት ነገር ቢኖር፤ በሴቶች ላይ ይህን የጭካኔ ተግባር በመፈጸማቸው፤ በቁመናቸው መገደላቸው መሆኑን ነው። ለምሳሌ አንድን ሰው ለፍላፊ ሆነሃልና፤ ምላስህ መቆረጥ አለበት ተብሎ ቢቆረጥ፤ እድሜውን ሁሉ ዲዳ እንደሚሆን ሁሉ፤ ሴትም በተገረዘች ጊዜ የሚሆነው ነገር ቢኖር፤ ከዚህ ያላነሰ ነው።

1- የፍትወት ስሜቷን በሙሉ ተቆርጦ ስለሚጣል፤ በሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ጊዜ፤ በቀላሉ እንዳትረካ ያደርጋታል።
2- ከባለቤቷና ከቤተሰቧ ጋር በሰላም እንዳትኖር፤ ነጭናጫና ቁጠኛ ያደርጋታል።
3- ከባሏ ውጭ ሌላ ወንድ እንድትፈልግ ይገፋፋታል።
4- በሩካቤ ሥጋ ውስጥ የሚገኘውን ደስታ እንዳትባረክበት ይከለክላታል።

እነዚህና ሌሎችም መሰናክሎች የሚፈጠሩት፤ ካለ ዕውቀት ከሚደረግ የሴቶች ግርዘት የሚመጣ ነው። የሚገርመው ነገር ቢኖር በአሁኑ ለአት፤ የአብዛኛው ባለትዳር ዋና ችግርም የሩካቤ ሥጋ አለመጣጣም መሆኑ ነው። በተለያዩ አገሮች ያለው ሕዘባችን ብሶቱ ይህ ስለሆነ፤ መፍትሄ በቶሎ ሊፈለግለት ይገባል። ብዙ ጊዜ ሰዎች ስለ ችግሩ ያወራሉ፤ መነሻውንና መፍትሄውን ግን ይዘሉታል። በዚህ ምክንያት ችግሩ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ፤ የማይ ነቀል ነቀርሳ በመሆን ዘርን ያከስማል። እገልጋዮችና የአገር መሪዎች፤ እንደ ኤልሳዕ ከምንጩ ላይ ብናተኩር፤ እውነተኛ ፈውስና በረከት ለምድራቱ እንዲመጣ ማድረግ እንችላለን። ጭንገፋንና መራራ ሕይወትን፤ ከሕዝቡ እናስወግዳለን።

ለ- ደባል ማስገባት ወይም ከቤተ ሰብ ጋር መዳበል

የኢኮኖሚና ሌሎች የተለያዩ ችግሮችን ምክንያት በማድረግ፤ በትዳር ላይ ተጨማሪ ሰው ማዳበል፤ በጣም ከባድ ችግር ነው። ይህ ዓይነቱ እርምጃ፤ ባልም ሆነ ሚስት ራሳቸውን በቤታቸው ውስጥ፤ በነጻነት እንዲዝናኑ እንቅፋት ይሆንባቸዋል። ለምሳሌ ስስ ጥጃማ /ልብስ/ መልበስ አይችሉም። እንደ ልብ መቀላለድና መተሻሸት /መዳራት/ አይችሉም። ቀላል የሆኑ ኩርፊያዎችን፣ ወዲያውኑ ተወ ያይተው እንዳያስወግዱ እንቅፋት ይሆንባቸዋል። ሌላም ሌላ ተጨማሪ ችግሮች አሉበት።

እንደ እኔ ሰውን ከጠባብ ቤታችሁ ውስጥ ጨምራችሁና ደርባችሁ፣ በፈቃዳችሁ ወደ ቁም እስር ቤት ከምትገቡ፣ ከምት በሉት ቀንሳችሁ በገንዘብ ብትረዱና፣ በነጻነት ብትኖሩ እመርጣለሁ። «በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻ አወጣን» ነውና ተመልሳችሁ በባርነት እትያዙ። ሱዳን በስደት በነበርኩበት ጊዜ፣ ከብዙ ሰዎች ጋር እብረን ስለኖርን፣ በእኔና በባለቤቴ ሕይወት ብዙ ችግሮች ተፈጥረውብን እንደነበር አልዘነጋውም። የሆነው ሆኖ ይህ ምክር እንጅ፣ የማይሻረው የሜዶንና የፋርስ ሕገ ደንብ ስላልሆነ፣ የሚመቻችሁን እድርጉ። እርግጥ ነው አዲስ ለተጋባችሁ ቢያንስ ቢያንስ አመት እስከሚሞላችሁ ድረስ፣ ሌላ ሰው ባትደርቡ ይሻላችኋል እላለሁ።

ከተጋባችሁ በኋላ ራሳችሁን ቻሉ እንጅ፣ ከቤተሰቦቻችሁ ወይም ከወላጆቻችሁ ጋር ደባል አትሁኑ። እንደዚህ የምታደርጉ ከሆነ፣ በትዳራችሁ በቀላሉ ችግር ይገጥማችኋል። ምክንያቱም ወላጆች በማንኛውም ነገር ለልጆቻቸው ስለሚያደሉ፣ ጣልቃ በመግባት ሊያስቸግሩ ይችላሉና ነው። ለማንኛውም በተቻለ መጠን እንዳቅ ማችሁ ራሳችሁን ችላችሁ ለብቻችሁ ለመኖር ጥረት አድርጉ።

ሐ- ፍቅርን ለሦስተኛ ሰው ማጋራት

ባልና ሚስት የራሳቸው የሆነ ልዩ ፍቅር አይነት አላቸው። ያ ፍቅር ለግበረ ሥጋ ግንኙነት የሚዳርግና የሚገፋፋ ነው። ብዙውን ጊዜ አብረው ብቻቸውን በሚሆኑበት ጊዜ፣ የሚጫወቱት ጨዋታና ቀልድ፣ አንድ ላይ የሚበሉት ምግብ ሁሉ፣ እየገፋ የሚወስዳቸው ወደ ሩካቤ ሥጋ ይሆናል። ይሁንና ልጅ በሚወለድበት ጊዜ፣ ወይም ወላጅ እብረው መቀመጥ በሚጀምሩበት ጊዜ፣ የፍቅሩና የጊዜው ሁኔታ ለሌላ ስለሚካፈል፣ በሩካቤ ሥጋ ላይ ትልቅ ችግር ይፈጥራል።

ምናልባት በብዙ ጥበቃ የመጣ ልጅ ከሆነ፣ በጣም ስለሚወደድ የባልን /የሚስትን/ ድርሻ ይሻማል። ብዙ ጊዜ ሳይታሰብ ነው

ይህ ዓይነት ችግር የሚፈጠረውና፤ የማንን ለማን እንደ ምትሰጡ ተረዱ። ጌታ እየሱስ « <u>የቄሳርን ለቄሳር፡ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር</u> » እንዳለው፤ ልጅና ወላጅ እንደ ስማቸው ዘመዶች ናቸው እንጂ፤ ባልና ሚስት ስላልሆኑ መጠንቀቁና ማወቁ ዘጥፋት ይጠብቃል።

በተለይም የእኛ ባሕል በብዙው ከወላጅ ጋር የተቆራኘ በመሆኑ፤ በጋብቻ ላይ ከፍተኛ ችግር መፍጠሩ አልቀረም። እናትና አባት ሁልጊዜ በልጃቸው ትዳር ላይ፤ የማዘዝ መብት ያላቸው መስሎ ይታያቸዋል። ትዳሩ እነርሱ በሚፈልጉት መንገድ የሄደ መ ስሎ ካልታያቸው፤ ብዙ ቀውሶችን ለመፍጠር ወደ ኋላ እንደማይሉ የታወቀ ሃቅ ነው። «ሰራ ከመፍታት ልጄን ላፋታት» የሚለው ኋላ ቀር ባሕላዊ መፈክር፤ «ሰራ ከመፍታት ልጄን ላስታርቃት» ቢሆን ያማረ ይሆን ነበር።

ወላጆች በዚህ አጋጣሚ ሊረዱት የሚገባ ጉዳይ ቢኖር፤ በሠርግ ቀን ልጃቸውን መርቀው መላካቸው በሕዘብ ፊት ኃላፊነት ማስወረዳቸው መሆኑን ነው። ልጆች ካገቡ በኋላ፤ የሚበጃቸውንና የሚጠቅማቸውን መወሰን የሚችሉ ሙሉ ሰዎች ናቸው። ስለዚህ ነፃነት ተነፍጓቸው ሁልጊዜ ልምራችሁ ሊባሉ አይገባም። ችግር ቢፈጠር እንኳ፤ የወላጆች ድርሻ፤ ያለ እድልአ ፍርድን በመስጠት ነገሮችን ማርገብ መሆን አለበት።

መ. ለግብረ ሥጋ ግንኙነት ቅድመ ዝግጅት አለማድረግ

ብዙ ጊዜ በማስተዋልም ይሁን ባለማስተዋል፤ ስሜትን የሚጎ ዱ ቃላቶች መናገር በአገራችን የተለመደ ነው። በተለይም ወንዶች በሴቶች ላይ በቀልድም ይሁን በቁም ነገር፤ ለሚናገሯቸው ቃላቶች ጥንቃቄ አያደርጉም። ስለዚህ ሴቶች ብዙ ስለሚጎዱ፤ ለባላቸው ያላቸው ፍቅር ይቀነሳል። በዚህ ምክንያት ሙሉ በሙሉ ማንነታቸ ውን ለባላቸው ለመስጠት ይቸገራሉ። ምክንያቱም የተወረወሩት መጥፎ ቃላቶች፤ ሁልጊዜ በጀሮአቸው ስለሚያቃጭሉባቸው ነው።።።

የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚፈጸመው ማታ በመኝታ ብቻ እይ ደለም። ከጧት ጀምሮ በሚወረወር ፈዋሽ ቃል ጭምር እንጂ። ቀን ስታንቋሽሻትና ስትሰድባት ውለህ፤ ማታ የግብረ ሥጋን ግንኙነት ለመፈጸም መሞከር፤ በሙት ባህር ውስጥ እንደ መዋኘት ያህል ይሆንብሃል። ተንሳፋፊው አንተው ራስህ እንጅ፤ ሚስትህ የትይንቱ ተካፋይ እንደማትሆን ተገንዘብ። ምክንያቱም፦ <u>ስሜቷ የተጐዳን ሴት ሩካቤ ሥጋ አይፈውሳትምና ነው።</u> ስለዚህ ከማለዳ ጀምረህ እስከ መኝታ ድረስ፤ የምትወረውረውን ቃል አስተውለህ እወቅ። ሚስትም ብትሆኝ እንደዚሁ ማድረግ ይገባሻል።

ሠ. ከቤተሰብ አለመማር

በአገራችን ያሉ ወላጆች ለልጆቻቸው ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙ ነት፤ ምንነት ትምህርት አይሰጡም። እንዲያውም ልጆቻቸው ግብረ ሥጋን የተመለከተ ጥያቄ ካቀረቡ፤ እንደ ባለጌና ስድ አደግ ተብለው ይወነጀላሉ። ይህ አይነቱ የባሕል ተጽዕኖ፤ ልጆቹን ፈሪዎችና ተጠራጣሪዎች እንዲሆኑ መንገድ ይጠርግላቸዋል። ስለዚህ ከወላጆቻቸው ያጡትን ከሌሎች መማር ስለሚፈልጉ፤ ያለጊዜያቸው ሳያስቡት ወደ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ይገባሉ። ስለዚህ ወጣት ሴቶች ጥንቃቄ ስለማያደርጉ፤ በድንገት ያረግዛሉ። ከዚያም የነበራቸው ተስፋ ሁሉ ይጨልምባቸውና ከወላጆችና ከዘመድ በመሸሽ፤ የተበላሸ ሕይወት ውስጥ ይዘፈቃሉ።

ሌሎቹ ደግሞ፤ ለእካለ መጠን ደርሰው ወደ ጋብቻ ሲሄዱ፤ ስለወሲብ ግንኙነት በቂ ዕውቀት ስለሌላቸው፤ ትዳራቸው የተዛባና ሰላም የጠፋበት መራራ ይሆንባቸዋል። ችግራቸውን እንኳ ገልጸው እንዳይናገሩ፤ ከወላጆቻቸው በሕጻንነታቸው የሰሙት ቃል ስለሚወ ቅሳቸው፤ "ባለጌ" እባላለሁ በመባል፤ አፍነው በመያዝ ይጨነቃሉ። እንደዚህ አይነቱ ችግር ከዘር ወደ ዘር እየተላለፈ በመሄድ፤ የአገራ ችንን የትዳር ብርሃን አጨልሞታል።

ለአንዲህ አይነቱ ችግር፣ በቶሎ መፍትሄ መፈለግ ተገቢ ነው። ስለዚህ ወላጆች፣ ልጆች ለአካለ መጠን መድረስ ሲጀምሩ፣ እ ናቶች ለሴት ልጆቻችሁ፣ አባቶች ለወንድ ልጆቻችሁ፣ ትምህርት መስጠትን ጀምሩ። የወሲብ ፍላጎት፣ እድሜን ጠብቆ የሚመጣ የእግዚአብሔር ስጦታ በመሆኑ፣ ሊያሳፍራችሁና ሊያስደነግጣችሁ አ ይገባም። ይልቁንም በግልጽ ልጆቻችሁን ጥቅምና ጉዳቱን በግልጽ ብታስረዷቸው፣ ከብዙ ጉዳት ትጠብቋቸዋላችሁ። «ምክር ከሌለች ዘ ንድ የታሰበው ሳይሳካ ይቀራል።» ምሳ 15፣ 22

7-3 የባሕርይ ስሰመግባባት

ሀ- የውይይት ችግር

በሩካቤ ሥጋ ላይ ችግር ከሚፈጥሩት ውስጥ አንዱ፣ ጤናማ ውይይት በባልና ሚስት መካከል አለመኖሩ ነው። የተለያዩ ችግ ሮች በቤተሰብ በሚፈጠሩበት ጊዜ፣ በኃይል ወይም በቁጣ መፍትሄ ለመስጠት ስለሚታሰብ፣ ለውይይት ቦታ አይሰጠውም። ከአስተዳ ደግ ወይም ከባሕል የመጣ የቁጣ ልምድ፣ በቶሎ መቀጨት ያስፈ ልገዋል።

«ቁጡ ሰው ጠብን ያነሳሳል፣ ትዕግሥተኛ ሰው ግን ጸጥ ያስ ኘዋል።» ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። ምሳ 15፣18 ባልና ሚስት ጤና ማ ትዳር መኖር ከፈለጉ፣ የውይይት አድማሳቸውን ማስፋት ይገባ ቸዋል። በቤት ውስጥ ለሚወሰነው ትልቅም ይሁን ትንሽ ጉዳይ፣ ባ ልና ሚስት መወያየት ይጠበቅባቸዋል። የመደማመጥና የመከባበር ስሜት የግብረ ሥጋን ግንኙነትን ጣፋጭ ያደርገዋል። ስለዚህ ባልና ሚስት፣ እርስ በእርሳችሁ ተወያዩ። የዝምታን ዱላ ከቤታችሁ በማስ ወገድ፣ የደስታን ምስጢር በውይይት ተለማመዱ።

ለ- የሌላውን ፈቃድ አለማክበር

በተለይ የመጀመሪያው ቀን በተደረገው ግንኙነት፤ ወይም ክ ብረ ንጽህና ሲወሰድ ማለት ነው፤ በኃይልና በጉልበት ከተደረገ፤ በሴቷ ውስጥ የአካል ህመም ያስከትላል። ይህ ደግሞ መጥፎ ትዝ ታ ስለሚያስቀምጥባት፤ የሩካቤ ሥጋ ፍላጐቷን እሚጠ ይወስደ ዋል። በተለይ በገጠር በህጻንነታቸው በሚዜዎች እግሯ ተይዞ ሕጓን ለመውሰድ የሚደረገው ኋላ ቀር ስርአት፤ ትልቅ ጭካኔያዊና እንስ ሳዊ ተግባር ነው። መቅረት ያለበት መጥፎ ባሕል ነው። የገጠር ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች፤ ይህን ተግባር ማስተው ይጠበቅባቸዋ ል። አብዘኛዎቹ የአገራችን የገጠር ሴቶች፤ ከባላቸው እየሸሹ ወደ ከተማ በመግባት ሴተኛ አዳሪዎች የሚሆኑት፤ ከዚህ የተነሳ አንደ ሆነ ለሁሉም ግልጽ ነው።

እዚህ ላይ ባል መጠንቀቅ ያለብዘ፤ ሚስትህ የግብረ ሥጋ ፍ ላጎት ከሌላት፤ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሆን ይችላልና ሁኔታዎችን መርምራቸው። ምናልባት ከአንተ በፊት ክብረ ንጽህናዋ ተወስዶ ከነበረ፤ ችግሩን በመረዳት ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልግሃል። ወይም አንተ ራስህ በመጀመሪያው ቀን በጉልበት ተጠቅመህ ተገናኝተሃት ከሆነ፤ ትልቅ ጉዳት በአእምሮዋ አስቀም ጠሃልና ንስሐና ይቅርታ በመጠየቅ፤ ደግመህ ተመሣሣይ ድርጊት እንደማትፈጽምባት፤ በቃልና በሥራ በመግለጽ ለማሳመን ሞክር። ካልሆነ ግን ፈቃደኛ ባልሆነችበት ጊዜ፤ በኃይል አታስገድዳት። ልብ በል ላንተም የግብረ ሥጋ ፍላጎትህ ጤናማ የሚሆነው፤ ፈቃዷ ን ሙሉ በሙሉ ሚስትህ ስትሰጥህ ብቻ ነው።

ሐ- የእንቅልፍ ጊዜን መረበሽ

አንቅልፍ ለሰው ልጅ በጣም አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሳ፤ የ ሰውን ጤንነት አማካይ ሆኖ እንዲጓዝ የማድረግ ኃይል አለው። ለ ዚህም ነው ተመጣጣኝ ወይም በቂ አንቅልፍ ያላገኙ ሰዎች የሚታ መሙት። ይህም ብቻ አይደለም፤ አንቅልፍ ማጣት ጠባየ ነጭና ጫና አመል የለሽ ያደርጋል። ብዙ ወንዶች ይህን ስለማይረዱ መስ

ለኝ፤ በውድቅት ሌሊት ከአፍላ እንቅልፍ ላይ ሴቶችን ቀስቅሰው፤ ሰሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ሚስቶቻቸውን ዕረፍት ይነሳሉ። የዚህ ዓይነት ድርጊት የግበረ ሥጋን ፍላጐት ከመቀነሱም በላይ፤ ሚስት በባልየው ላይ ከፍተኛ ጥላቻን እንድትፈጥር ያደርጋታል። እንቅልፍ ማለት ሕይወት ማለት ነው።

እስኪነጋ መታገስ ያቃተው ወንድ፤ የወደፊት ትዳሩንና የልጆቹን ሕይወት ያናጋል። በጣም አጥብቀን ልንገነዘበው የሚገባ ነገር ቢኖር፤ እንዳንድ ሰዎች እንድ ጊዜ ከነቁ በኋላ ተመልሰው ለመተኛት፤ በቀላሉ እንቅልፍ የማይወስዳቸው እንዳሉ ነው። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች በጥንቃቄ ካልተያዙ፤ የጭንቀት በሽታ በቀላሉ ያጠቃቸዋል። ሰይጣንም ክፉ መንፈስን በውስጣቸው በማብቀል፤ ወደ ሞት ሊያደርሳቸው ይችላል። የዚህ ዓይነት ችግር የገጠማቸው ቤተሰቦች ገጥመውኛልና ይታሰብበት። ሚስትህ ሁልጊዜ ያንተ ናት። ልዩ ጥንቃቄና እንክብካቤ አድርግላት። ከሁሉ በፊት ለማንነቷ ትልቅ አክብሮትና ቦታ ስጣት። ለሁሉም ጊዜ እንዳለውም አትዘንጋ።

መ. ሆድና ጀርባ መሆን

ያልተመጣጠነ ፍቅርና የዕድሜ ደረጃ፤ ባልና ሚስትን ሆድና ጀርባ ያደርጋቸዋል። በዚህም ምክንያት የወሲብ ፍላጎታቸው እየተቃረነ እንዲሄድ ይገደዳል። ምክንያቱም፦ <u>አንዱ ሰጪ ሌላው ተቀባይ ብቻ ስለሚሆን ነው</u>። በእርግጥ ነው ወንድ ዘር ይሰጣል፤ ሴት ትቀበላለች። ያን ማለቴ አይደለም። ነገር ግን ንግግርንና ሙገሳን በተመለከተ፤ ብዙውን ጊዜ ምላሽ አይሰጡም። <u>ለምሳሌ</u>፦ ባል ሚስቱን በስው ፊትም ይሁን ለብቻ፤ እንደሚወዳትና እንሚያከብራት አሳቡን ሲገልጽ፤ በንቀት ወይም በትዕቢት መመልከትና ማቃለል፤ ተገቢ ካለመሆኑም በላይ፤ የሩካቤ ሥጋን ስሜት ይቀንሳል። ወይም ሴት ባሏን ማሞጋገስ ስትጀምር፤ ባል ድርጊቷን ባለመቀበል፤ እሰቧን ማንቋሸሽና ማዋረድ የመሳሰሉት፤ ክፉ በሽታዎችና መርገሞች ናቸው።

የዚህ ዓይነት ችግር ያለባቸው ሰዎች፤ ብዙውን ጊዜ ፍቅ ራቸው እኩል ያልሆኑ ተጋቢዎች ናቸው። እንዱ ክፍል በጣም ከመ ውደዱ የተነሳ፤ ማንነቱና መብቱን ሙሉ በሙሉ ለትዳር ጓደኛው አሳልፎ ሲሰጥ፤ የተወደደው ሰው በትዕቢት እንዲወድቅ ያደርገ ዋል። ደግሞም ከሚገባው በላይ ስለተቀበለ መሸከም ያቅተውና፤ ያ ቅበጠብጠዋል። ስለዚህ የንቀትና የግድ የለሽነት መልስ ለመስጠት ይደፍራል። ይህ ሰው አንድ ቀን በጌታ እጅ ሲወድቅ፤ ምን እንደ ሚመልስ አላውቅም።

የዚህ አይነት ችግር ላለበት ሰው ያለኝ ምክር፤ በተወደ ድክበት መጠን ያህል የሚጠሉህና ዐይንህን ማየት የማይወዱ ሰዎች በምድር ላይ እንዳሉ ተገንዘብ። እነዚያ ሰዎች ቢያገኙህ እያቆላመ ጡ እንደማይጠሩህ እወቅ። ቢቻላቸው ከምድረ ገጽ ሊያጠፉህ የሚ መኙ ናቸውና። ስለዚህ የምትወድህና የምትጠነቀቅልህ ሴት፤ ጌታ ስለሰጠህ እመስግነው እንጅ፤ ለመጥፋት እትታበይ። « ፍራ እንጅ የትዕቢትን ነገር እታስብ » ነውና።

ሚስትም ብትሆኝ፤ ባልሽን የወደደሽን ያህል የሚጠሉሽ መብዛታቸውን መገንዘብ ይገባሻል። የሆነው ሆኖ፤ በባለትዳሮች መ ካከል ተመጣጣኝ ፍቅር መኖሩ፤ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ውበትና ጣዕም ከመስጠቱም አልፎ፤ የቤተሰቡን ዕድገት ያፈጥነዋል። ይህ ሳ ይሆን ሲቀር ግን፤ ባልና ሚስት በመኝታ እንኳ ሳይቀር፤ ሆድና ጀ ርባ ሆነው ነው የሚተኙት። አንዱ ወደ ግድግዳ ሌላው ወደ ላሎን ዞረው ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች በቶሎ መፍትሄ ካላገኙ ለብዙ ፈተናና ችግር ይጭለጣሉ።

፯-4 የጤና ችግር

በተለያዩ የጤና ችግሮች ምክንያት፣ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ችግር ላይ ሊወድቅ ይችላል። አንዳንዶቹ ከስንፍናና ከዕውቀት ማነስ የመጡ ሲሆኑ፣ አንዳንዶች ግን በተፈጥሮ የሚመጡ ናቸው። ለማንኛውም ጥቂቶችን የጤና ችግሮች፣ ከነመፍትሄያቸው እንጥቀስ ።

ሀ- የአፍ ሽታ

ብዙ ጊዜ ትኩረት የማይሰጥበት፣ ነገር ግን የብዙ ባለትዳሮች ከፍተኛ ችገር የሆነው፣ የአፍ ሽታ ነው። በተለይ በስለጠነው አገር የሚገኘው ምግብ አብዛኛው በኬሚካል የተቀመመ ስለሆነ፣ ለአፍ ልዩ ሽታን ይፈጥራል። በአገር ቤትም ቢሆን በየቀኑ አፍን ጠዋትና ማታ መታጠብ ብዙም ስላልተለመደ፣ ተመሳሳይ ችግር አለ። በባሕ ል ምክንያት አፍሀ/ሽ/ ይሸታል ብሎ መናገር፣ እንደ ማዋረድ ስለ ሚቆጠር፣ ባልም ሆኑ ሚስት ችግሩን በግልጽ ለመናገር አይደፍ ሩም። እንዲህ አይነቱ ችግር የሚጎዳው፣ ጓደኛን ብቻ ሳይሆን፣ ራ ሱን አፉ የሚሸተውንም ሰው ጭምር ነው። ምክንያቱም የገዛ አፉን ስለማያሸት፣ ያለበትን ችግር ማስወገድ አይችልምና ነው።

ልብ በሉ! «አዳምና ሔዋን ራቁታቸውን ነበሩ አይተፋፈሩም ነበር» ሲል፣ ሁሉም ባልና ሚስት፣ የእነርሱን ፈለግ ይከተል ማለቱ ነው። አራቁት መሆን ለሁሉም ችግር ዘለቄታ ፈውስ ያስገኛል። የገዛ አካልህን/ሽን/ ገበና ካልነገርክ/ሽ/፣ ማን ሊያርምልህ/ሽ/ ትፈልጋ ለህ/ሽ/? ደግሞም እንዲህ ዓይነት ችግር የሁሉም ሰው ስለሆነ፣ በግ ልጽ መወያየቱ በጣም ጠቃሚነት አለው። የአፍን ሽታ ችግር መወ ያየቱ የግብረ ሥጋን ግንኙነት ብቻ ሳይሆን የሚፈውሰው፣ ጠቅላላ የአለት እለት ግንኙነትን ጭምር ነው።

እኔና ባለቤቴ በግልጽ እንደዚህ አይነቱን ችግር ስለምንወያይ፣ መፍትሄውን ለመፈለግ ጊዜ አልወሰደብንም። መጽሐፍ ቅዱስ፡- «ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ፣ በፍቅር ፍርሃት

የለም፤ ፍርሃት ቅጣት አለና፤ የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደ ለም» 1ኛ ዮሐ. 4፡18 በማለት ስለጤናማው የፍቅር ግንኙነት ያስገነ ዝበናል። የሚስትህን ችግር ለመግለጽ አትፈር። ሚስትም የባልሽን ችግር ሌላ ሰው እስኪነግረው አትጠብቂ። አካልሽ ነውና ጥበብ በተ ሞላው አነጋገር፤ ባልሽን በመምከር አቃኝው።

ለአፍ ሽታ መፍትሔው፦

የአፍ ሽታ በራሱ በሽታ ባይሆንም፤ የተለያዩ በኽታዎች ምልክት ሊሆን ስለሚችል፤ ጽዳትን በመጠበቅ ካልተወገደ ባለሙያ ማማከ ሩ ይመረጣል። በቀላሉ የሚወገድበት መንገዶች እንደሚከተሉት ተቀምጠዋል፤፤

1. በማለዳና በማታ ጥርስን መታጠብ

2. መጥፎ ሽታን የሚያጠፉ የሚገመጠመጥ መድኃኒት ስላለ፤ በእ ርሱ በመጠቀም ሽታን ማጥፋት። ስሙም ሊስተሪን /Listerine/ ሲባል፤ በማንኛውም መድኃኒት ቤትና ትልልቅ ግሮሰሪ ውስጥ ይገኛል። በተለይም በሰለጠኑት አገሮች ውስጥ በብዛት ይገኛ ል።

3. በአፍ ላይ የሚረጭ ትንሽ መድኃኒት በመግዛት፤ እርሱን ሁል ጊዜ በመያዝ መጠቀም። ማስቲካም ማኘክ ያግዛል።

ለ- እንኩርፊያ

ከአፍ ሽታ በመቀጠል ሊጠቀስ የሚገባው ሌላው ችግር ደግ ሞ፤ በእንቅልፍ ሰዓት የሚመጣው ኩርፊያ /ማንኮራፋት/ ነው። ይህ ችግር አሁንም ለሚያንኮራፋው ሰው አይታወቀውም። አብሮ ለሚተ ኛው ሰው ግን ትልቅ ችግር ነው። ስለዚህ ይህን ሁኔታ በግልጽ ተወያይቶ የሕክምና መፍትሔ መፈለግ፤ ከአደጋ ይጠብቃል።

ብንግረው ይቀየመኛል በማለት፤ ሚስት ራስሽንና ትዳርሽን አትጉ ጅ። ባልም በሚስትህ ላይ ያለውን ችግር ለመናገር ወደ ኋላ አት በል። እዚህ ላይ በሁሉም የትዳር ጓደኛሞች ሊታወቅ የሚገባው ቁም ነገር ቢኖር፤ እርማቱ ከጥላቻና ከተንኮል የማይሰነዘር መሆኑ ን፤ በንጹህ ልብ መረዳት እንደሚያስፈልግ ነው። ስለዚህ ምክሩ ሁሉ በምስጋና ምላሽ ማግኘት ይገባዋል።

ላለማንኮራፋት መፍትሔው፦

ማንኮራፋት በራሱ በሽታ ባይሆነም የተለያዩ በሽታዎች ምልክት ሊሆን ስለሚችል፤ ችግሩን ለሐኪም ማማከር አስፈላጊ ቢሆንም፤ በ ድካምና በቀን ውሎ ውጣ ውረድ የመጣውን ግን፤ ለማስወገድ የሚ ከተሉት ይመከራሉ።

1. ተለቅ ያለ ትራስ መግዛትና መንተራስ።
2. ለሃኪም ማማከር። መድኃኒት ስላለው በቀላሉ ማስወገድ ይቻላል።
3. መጻለይም ችግሩን ያስወግዳል። ማለትም ጌታ ሆይ የማንኮ ራፋት ችግር አለብኝና፤ ከእኔ አስወግድልኝ በማለት፤ በግል ጽ ስሙን ጠርቶ መጸለይ ፈውስን ያመጣል ብየ አምናለሁ ።

በእንደዚህ አይነት መንገድ ችግሩ በቶሎ ካልተቀጨ፤ የማያ ንኮራፋው ሰው እንቅልፍን ስለሚያጣ፤ አብሮ የመተኛት ስሜቱን ይጐዳበታል። ያም ብቻ ሳይሆን የራስ በሽታ ህመምና የጤና መታወክ፤ እንቅልፍ ባልተኛው ሰው ላይ ያይልበታል። በዚህም ምክ ንያት በቤት ውስጥ በሽታ ስለሚገባ፤ ትዳሩ በቀላሉ በጠላት ይጠ ቃል።

መ- የአካል ንጽሕና

በተገቢው ጊዜና ሰአት የራስን ንጽሕና አለመቆጣጠር፤ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ላይ ከፍተኛ ችግር ይፈጥራል። በዚህ ጉዳይ ወንድም ሴትም ተጠያቂ ናቸው። እንዳንዱ ከሥራ ብዛት የተነሳ ስለሚደክምና ከመተጣጠብ ይልቅ ማረፍን ስለሚመርጥ ነው። ሌላው ደግሞ ለንጽሕና የሚያስፈልጉት ቁሳቁሶች ተሟልተው ባለመገኘታቸው፤ ንጽሕናን ያጓድላሉ።

ለማንኛውም የጎሉትን ችግሮች፤ ከዚህ በታች እንመልከታቸው፦

የወንዱ ችግር፦

ሀ- ከሥራ ውሎ በሚመጣበት ጊዜ፤ ጠረን ያለውን ጫማ በመኝታ ቤት /በሳሎን/ በማውለቅ የቤቱን መዓዛ መቀየሩና፤ የሚስቱን ፍላጎት መቀነሱ

ለ- እንዲሁም እንዳላበው ውሎ፤ ሳይታጠብ ከነጠረኑ ሚስቱን ለማቀፍ መሞከሩ

ሐ- ልብሶቹንና የተለያዩ እቃዎችን፣ በግድለሽነት በየቦታው ማዝረክረኩ፤ ማለትም እንደ ውስጥ ሱሪና ከነቲራ፣ የእግር ሹራብ ወዘተ

እነዚህ ተግባሮች የሚስትን ስሜት በኃይል ስለሚጎዱ፤ ለግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳትነሳሳ እንቅፋት ይሆኗታል። በየቀኑ እንደ ቀላል እየታዩ የሚታለፉትን ጉዳዮች፤ ቦታ ሰጥቶ ማረሙ የትዳርን ሕይወት እንዲጣፍጥ ያደርጉታል።

የሴቷ ችግር፦

ሀ- ምግብ ስታዘጋጅ ቆይታ፤ ከብዙ ሽታ ጋር ላትታጠብ መተኛት

ለ- ቅቤን የመሳሰለ ቅባት ራስ ላይ ተቀብታ፤ መታቀፍን መፈለግ

ሐ- ሕጻናትን አጸዳድታ ሳትታጠብ፣ ባሏ እንዲያቅፋት ማሰብና ወዘተ. ናቸው

አንደነዚህ አይነት የጥንቃቄ ጉድለቶች፣ የባልን የወሲብ ፍላጎት በጣም ስለሚቀንሱት፣ ሴቶች በተቻለ መጠን በባሎቻችሁ ፊት በንጽና ለመቅረብ ተጣጣሩ። ሽቶዎችም ከውጭ ይልቅ በቤት ውስጥ ለባል ቢረጩለት፣ የበለጠ እንድትወደዱ ያደርጉአችኋል። ስለዚህ ባሎቻችሁ ወደ ቤት መምጫቸው መዳረሱን ስታውቁ፣ ስስ ልብሶችን በመልበስ፣ በመልካም ጠረን ለመቀበል ዝግጅት አድርጉ። የመኖራችሁ ትርጉም ባሎቻችሁ እንደሆኑ አትዘንጉ። ባጠቃላይ ንጽሕናን መጠበቅ ለራስ ብቻ ሳይሆን የሚጠቅመው፣ ለትዳር ጓደኛም ጭምር ነውና፣ ልዩ ትኩረት እንድትሰጡት አደራ እላችኋለሁ።

መ- ተጻብዖ /በእንቅልፍ ልብ ከመናፍስት ጋር መገናኘት/

ይህ አይነት ችግር፣ በእንቅልፍ ላይ እያሉ ከአጋንንት ጋር የሚደረግ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ሲሆን፣ በጣም አደገኛና ከፉ የትዳር ጸር ነው። በአገራችን አብዛኛው ሕዝብ ቆሌና አድባርን ስለሚያመልክ፣ ልጆቹንና ራሱን በስለት መልክ ለአጋንንት ይሰጣል። በዚህ ምክንያት ክፉው መንፈስ፣ ቢፈልግ ባል ወይም ሚስት በማድረግ፣ እንደፈለገ ይጫወትባቸዋል። በእንዲህ አይነት እስራት ውስጥ ያሉ ትዳር ቢዙም አይሰምርላቸውም። ምክንያቱም አጋንንቱ በፈለገ ጊዜ ስለሚገናኛቸው፣ ለትዳር ጓደኛቸው ፍቅር አይኖራቸውም።

በዚህ ምክንያት ትዳርና ቤታቸውን በማፍረስ፣ ሴተኛ አዳሪዎችና ብኩኖች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ይህን አይነት ችግር ላለባቸው መፍትሄው፣ በጌታ እየሱስ ስም ከአጋንንቱ እስራት ነጻ መውጣት ነው። አጋንንቱ ካልወጣ ግን፣ በሕይወታቸው ላይ ሳይቀር አደጋ ያደርስባቸዋል። ስለዚህ ሁኔታ በሰፊው የሚያስረዳውን

(ስይጣን ሲጋለጥ) የተባለውን፤ በፓስተር ሠይፉ ከበደ የተጻፈውን መጽሐፍ፤ እንዲያነቡ በጥብቅ እመክራለሁ። መጽሐፉ ለዚህ አይነት ችግር ፍቱን መድኃኒት ይሰጣልና ነው።

እርግጥ ነው ዳግም ተወልደው በጌታ እየሱስ አዲስ ፍጥረት የሆኑ ሁሉ፤ የዚህ አይነት ችግር ብዙም አያጠቃቸውም። ይሁን እንጅ አልፎ አልፎ ከዘር የተላለፈ መርገም ሊጠናወታቸው ስለሚችል፤ ማወቁና መጠንቀቁ ትዳርን ከማፍረስ ይከላከላል። በዚህ አይነት ችግር ውስጥ ያላችሁ አማኞች ካላችሁ፤ ወደ መንፈሳዊ መሪዎች በመቅረብ፤ መንፈሳዊ ምክርና ጸሎት ብታገኙ መልካም ነው እላለሁ። ለማንኛውም የጌታ እየሱስ ስም፤ የአጋንንት ሥራ ስለሚያፈርስ፤ በጌታ እየሱስ ስም መንፈሱን በመቃወም ከእናንተ አስወግዱት።

ሠ. ሕመም

አዳምና ሔዋን በኃጢያት ከወደቁ ጀምሮ፤ በሽታ የሰውን ዘር በሙሉ በመውረር ያንገላታል። የሞቀ ትዳር ይዘው በሚኖሩ ፍቅረኞሞችም መካከል ጣልቃ በመግባት፤ ቤትን ያፈርሳል። አንዳንዱ በሽታ በቀላሉ ሲፈወስ፤ ሌላው ደግሞ ጊዜ የሚጠይቅ ይሆናል። አንዳንዱ የበሽታ አይነትም የወሲብን ፍላጎት ስለሚቀንስ፤ የትዳር ጓደኛን ይጎዳል። ጤነኛው የትዳር ጓደኛ ትዕግሥት ካላገኘ በስተቀር፤ በቀላሉ ወደ ፍች ሊያመራ ይችላል።

ይሁን እንጅ ቃል ኪዳን እስከሞት ድረስ በመሆኑ፤ ባልና ሚስት ታማኞች ሆነው፤ ጓደኞቸውን ማስታመም ይገባቸዋል። ጌታ ሁሉን ቻይ በመሆኑ፤ በጸጋ ጸሎት በመቅረብ ፈውስን ማምጣት ይቻላል። የኢዮብን ሚስት ይመስል በችግር ጊዜ ጥሎ መሸሽ ተገቢ አይደለም። የታመመ ይፈወሳል። ያዘነም ይጽናናል። ጌታ ለሁሉም ችግር መፍትሄ መስጠት ይችላል። ስለዚህ በታማኝነት ወደ እርሱ መጮሁ ተገቢ ነው። በሆነ ባለሆነው አላቦ ወደ ፍች መሰማራቱ፤

ትልቅ ኃጢያት በመሆኑ ዋጋ ያስከፍላል። ስለዚህ በዚህ አይነት ችግር ያላችሁ ባልና ሚስቶች፤ ጌታን በመጠበቅ እንድትታገሱ እመክራለሁ።

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ ያየናቸው፤ ዋና ዋና የግብረ ሥጋ ግንኙነት ችግሮች ናቸው። ባልና ሚስት እንዚህን መሰናክሎች አስቀድሞ በማወቅ መጠንቀቅና ማስተካከል ይገባቸዋል። ከሁሉም በላይ በጌታ ፊት አብሮ በጸሎት በመቅረብና፤ ግልጽ ውይይት እርስ በእርስ በማድረግ፤ ፍቅርን ማዳበር ያስፈልጋል። ስለዚህ ይህን ለማ ድረግ ሁላችሁም ጥረት እንድታደርጉ በማሳሰብ፤ ወደ ሚቀጥለው ርእስ እንሸጋገር።